## ምዕራፍ ፲

### በደብረ ዘይት ምንባብ

፩ ክርስቶስ አምላኪየ ወተስፋየ ወስመ አቡሁ ጌራ መድኃኒትየ፡ወስመ መንፈስ ቅዱስ ነቅዓ ቅድሳትየ፡ሞገሰ መስቀሉ አክሊለ ትምክሕትየ ወእግዝእትነ ማርያም መራኅተ ገነትየ፡፡ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ዓዘቅተ ጥምቀትየ፡ ወሐዋርያት መጥምቃንየ፡ ወቅብዐ በለሳን ማኅተመ እምነትየ፡ ወገድለ ኵሎሙ ቅድሳን መስተሥርየ ኃጢአትየ፡ ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

፪ አንሰ እፈቅድ ክርስቲያን እሰመይ ወክርስቲያን እህሉ፡ክርስቲያን እዓል ወክርስቲያን እቢት በኵሉ መዋዕለ ሕይወትየ በከመ ትምህርተ አበውየ ሐዋርያት፡፡ወክርስቲያን እኑም ውስተ ከርሠ መቃብር ከመ አበውየ ሐዋርያት፡፡ወክርስቲያን እንቃህ በተንሥኦትየ ምስለ አበውየ ሐዋርያት፡፡ወክርስቲያን እርፍቅ በደብረ ጽዮን ቅድስት ውስተ ሕፅነ አበውየ ሐዋርያት፡፡ፍቅር ያጌብረኒ ነጊረ ዜናሆሙ ለቅዱሳን፡፡ወቅንዐት ያጌብረኒ ከመ እሰብሖ ለክርስቶስ፡፡ወቅንዐት ያጌብረኒ ከመ አውግዞ ለሰይጣን፡፡ፍቅር ያጌብረኒ ከመ እትልዎሙ ለሐዋርያተ ክርስቶስ፡ወቅንዐት ያጌብረኒ ከመ አጕይዮሙ ለረሲዓን፡፡ፍቅር ያጌብረኒ ከመ እጽአሎሙ ለማርያን፡፡

፫ ኀበ ተከዕወ መዓዛ ዕፍረቱ ለኢየሱስ ክርስቶስ ህየ ይጼኑ መካን በጼና ሠናይ መዓዛ፡፡ኀበ ተከዕወ ውኂዘ ትምህርቶሙ ለዕልዋነ ሃይማኖት ህየ ይጸይእ ጼና ጺአቱ ለሰይጣን፡፡እስመ ዘይገስስ አፈወ ይምዕዝ እዴሁ በእንተ ዘለከፎ ለርኄ አፈው፡፡ ወዘሂ ገሰሰ ፍጉገ ይጸይእ እዴሁ በእንተ ዘገሰሶ ለጽዩእ፡፡ኀበ ዘይትናገሩ ዘመለኮት ህየ ሀሎ እግዚአብሔር፡ ኀበ ዘይትናገሩ ዘስህፀተ ዕልዋን ህየ ይጼዐቁ አጋንንት፡፡ወይእዜኒ ንንግር ዘለፋሁ ለቢቱ ዘይክሕድ ምጽአተ አብ ወይብል ይመጽእ ወልድ ዘእንበለ አብ ለፍዳ ኃጥአን ወለዕሤተ ጻድቃን፡፡እትሔዘብ አንሰ በእንቲአሁ ከመ ውእቱ ሰይጣን ሥጋው ወጋኔን ስቡእ፡፡

## ምዕራፍ ዐሥር

### የደብረ ዘይት ምንባብ

፩ ክርስቶስ አምላኬና ተስፋዬ ነው የአባቱም ስም የመድኃኒቴ ዘውድ ነው የመንፈስ ቅዱስም ስም የቅድስናዬ መገኛ ነው፡፡ እመቤታችን ማርያም የገነት መክፈቻዬ ናት የከበረች ቤተክርስቲያን የጥምቀት ጉድጓዴ ናት ሐዋርያትም አጥማቂዎቼ የበለሳን ቅባትም የእምነቴ ማኅተም ነው የቅዱሳንም ሁሉ ገድል የኃጢአቴ ማስተሰረያ ነው ለዘላለሙ አሜን፡፡

፪ እኔ ክርስቲያን እባል ዘንድ ከክርስቲያንም ጋር ሆኜ እኖር ዘንድ በዘመኔም ሁሉ እንደ አባቶቼ እንደ ሐዋርያት ትምህርት ክርስቲያን ሆኜ እውል ዘንድ ክርስቲያንም ሆኜ አድር ዘንድ እሻለሁ፣ እንደ አባቶቼ እንደ ሐዋርያት ክርስቲያን ሆኜ በመቃብር ወስጥ ላንቀላፋ በምንጊዜም ጊዜ ከአባቶቼ ከሐዋርያት ጋር ክርስቲያን ሆኜ ልነቃ ክርስቲያን ሆኜ በከበረች በደብረጽዮን በአባቶቼ በሐዋርያት እቅፍ ልቀመጥ የቅዱሳንን ዜናቸውን ለመናገር ፍቅር ግድ ይለኛል፡ ቅንዐትም ከሀዲዎችን እንቅፋቸው ዘንድ ያስገድደኛል፡፡ ፍቅር ክርስቶስን እንዳመሰግነው ግድ ይለኛል፡ ቅናትም ሰይጣንን አወግዘው ዘንድ ያስገድደኛል፡፡ፍቅር የክርስቶስን ሐዋርያት እንድከተላቸው ያስገድደኛል ቅናትም ዝንጉዎችን እንድሸሻቸው ግድ ይለኛል፡፡ፍቅር ሰማዕታትን እወድሳቸው ዘንድ ግድ ይለኛል ቅናትም ጠንቋዮችን እንድ ዘልፋቸው- ያስገድደኛል፡፡

፫ የኢየሱስ ክርስቶስ የሽቱ መዓዛ በፈሰሰበት በዚያ ሥፍራ ያማረ መዓዛ ይሸታል ሃይማኖትን የካዱ የእነርሱ የትምህርታቸው ፈሳሽ በፈሰሰበት በዚያ የሰይጣን የክርፋቱ ሽታ ይከረፋል፣ ሽቱን የሚነካ እጁ ሽቱን ስለዳሰሰበት መልካም ጠረን ይሸታል ክርፋትን የነካ ግን የከረፋውን ስለዳሰሰበት እጁ ይከረፋል፣ የመለኮትን ነገር በሚናገሩበት ሥፍራ በዚያ እግዚአብሔር ይኖራል የከሀዲዎችን ክህደት በሚናገሩበት በዚያ አጋንንት ይጨነቃሉ፡ አሁንም የአብን መምጣት ክዶ ለኃጥአን ፍዳን ለጻድቃንም በጎ ዋጋን ለመስጠት ወልድ ያለ አብ ይመጣል ያለ የቢቱን ዘለፋ እንናገር፡፡ እኔስ ስለ ርሱ ሥጋን የለበሰ ሰይጣን ሰውም የሆነ ጋኔን እንደሆነ አስባለሁ፡፡

፬ እፎኬ ይብል እጓለ እመሕያው ዘመ
ጠነገ ጽረፈተ ላዕለ ዕብየ መለኮት፡፡ወዘመጠ
ነዝ ኩፋሌ ላዕለ መንግሥተ ወልድ ወወላዲ፡፡
ይመስለክሙኑ ዘኢየአምር ቢቱ መጻሕፍተ ነ
ቢያት ወሐዋርያት፡፡የአምርኬ ጥቀ ወባሕቱ
ይትግህ በዘያሠምሮ ለሰይጣን፡እስመ ሰይጣን
ኒ ኢኮነ ዘኢየአምር ትእዛዘ እግዚአብሔር አላ
ኮነ ዘይትቃወም ትእዛዞ በትዕቢተ ልቡ ወበአ
ንሥኦ ርእሰ ኀሊናሁ፡፡ሰይጣን ይትግህ በዘያ
ስሕቶሙ ለውሉደ ሰብእ እስመ የአምር ከመ
ያፈቅሮ እግዚአብሔር ለእጓለ እመሕያው፡፡ወቢ
ቱኒ ይትሜስል ከመ አቡሁ ሰይጣን ይትግህ
በዘያስሕቶሙ ለመሀይምናን፡እስመ አስሕቶቱ
ለሰይጣን ይቀልል እምአስሕቶቱ ለቢቱ፡፡ እስ
መ ሰይጣንስ ነኪር ውእቱ እምዘመድነ ወፀር
ለስብሐተ እግዚአብሔር ፈጣሪሁ፡፡ወቢቱሰ
ይሰሚ ርእሶ ክርስቲያናዌ ወበኀሊናሁሰ ኢክ
ርስቴን፡፡ይብል በኀሊናሁ ጥሙቅ አነ ወበሃይ
ማኖቱሰ ኢጥሙቅ፡፡ምንተኑ ንብል በእንተ
ቢቱ አርዌ ምድርኑ ንብሎ ለአርዌ ምድርኒ
ይልሕም እከዩ፡፡ወአርዌ ምድርሰ ኢያደውዮ
ዘእንበለ ለዘነሰኮ በአስናኒሁ፡፡ወቢቱሰ ይክል
አሕምሞቶ ለዘይቀርብ ኀቤሁ ወይትናበቦ በአ
ፉሁ ይወዲ ሕምዘ ውስተ ነገረ ሰላም ወይመ
ይጥ ተሰናእዎ ኅበ ለኳ፡፡ዘአንፈጸ ቀራንብቲ
ሁ እምንዋም ወኢይዴቅስ እመ ኢገብራ ለእ
ኪት፡፡በሊሕ አገሪሁ ለከዒወ ደም ወጽልሕው
ልሳኑ ለነቢበ እኪት፡፡ያነድድ ተዓይነ ዘእን
በለ እሳት ወያስተጣርህ ነገሥተ ከመ ንቃወ
አንበሳ፡፡ያአረውዮ ለየዋህ ከመ ድብ ሐራስ
ወይሬስዮ ከመ ሐራውያ ሐቅል ለዋው፡፡ ወአ
ልቦ ዘይብሎ ዘንተ ሐሰውከ ወዘንተ አሕሰምከ
እስመ ረከበ ሞገሰ በኀበ ሰይጣን፡፡ወንጉሥኒ
ይጥሕር ከመ አንበሳ በእንቲአሁ ወሶበ ይሬ
እዩ ኢይክል አሕስሞ ላዕሌሁ፡፡

፭ ወይእዜኒ ኢንክል ፈጽሞ ነጊረ እከዩ
ለቢቱ በከመ ኢይትከሀል ፈጽሞ ነጊረ ዕበየ
ኂሩታ ለማርያም፡፡ወይእዜኒ ንንግር ዘለፋ ሃ
ይማኖቱ ወኢንጠናቀቅ በእንተ ነጊረ እከየ ም
ግባሩ፡፡በከመ ይቤ ጳውሎስ እስመ ሀለወነ ለ
ኩልነ ንትሐተት ቅድመ ምኲናኑ ለክርስቶስ
፡፡ዝ ውእቱ እበደ ትምህርቱ ለቢቱ ይቤ ይመ
ጽእ ወልድ ዘእንበለ አቡሁ፡፡ለአብሰ ረሰዮ
ከመ ንጉሥ ወወልድኒ ረሰዩ ከመ መልአከ ኃይ
ል፡ ከመ ይፌኑ ንጉሥ ርእሰ ሐራሁ ከመ

፬ የሰው ልጅ እንደምን በመለኮት
ላይ ይህን ያህል ስድብ ይህን ያህልም መከፋ
ፈልን በወልድና በወለደው ላይ ይናገራል፡፡ቢቱ
የነቢያትና የሐዋርያትን መጽሐፍ የማያወቅ
ይመስላችኋልን፡፡ፈጽሞ ያውቃል ነገር ግን ሰይ
ጣንን ደስ በሚያሰኘው ገንዘብ ይተጋል ሰይጣ
ንም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የማያውቅ አይ
ደለም እኮን፣ በልቡ ትዕቢት የኀሊናውንም ራስ
ቀና ቀና በማድረግ ትእዛዝን ይቃወማል እንጂ፡፡
ሰይጣን እግዚአብሔር የሰውን ልጅ እንደሚ
ወድደው ስለሚያወቅ የሰው ልጆችን ያስታቸው
ዘንድ ይተጋል ቢቱም አባቱ ሰይጣንን ይመስ
ላል፡ምእመናንን ያስታቸው ዘንድ ይተጋል የሰይ
ጣን ማሳት ከቢቱ ማሳት ይቀላልና፡፡ሰይጣን ከወ
ገናችን የተለየ ነው ለፈጣሪው ለእግዚአብሔር
ምስጋናም ጠላት ነው፡፡ ቢቱ ግን ራሱን የክርስ
ቲያን ወገን ብሎ ይጠራል በልቡ ግን ክርስቲያን
አይደለም በአሳቡ የተጠመቅሁ ነኝ ይላል በሃ
ይማኖቱ ግን ያልተጠመቀ ነው ስለ ቢቱ ምን
እንናገራለን እባብ ነው እንለዋለን እባብም እኮ
ለክፋት ይለሰልሳል፣ እባብስ በጥርሱ የነከሰውን
ካልሆነ በቀር ሌላውን አያቆስልም ቢቱ ግን
ወደርሱ የሚቀርበውን ማሳመም ይችላል
በአንደበቱም ይነጋገረዋል በሰላማዊ ነገር ውስጥ
መርዝ ይጨምርበታል፡ መስማማትንም ወደ
ጠብ ይለውጣል ሽፋሽፍቶቹን ከሽልብታ የከለከለ
ነው ኃጢአትንም ካልሠራት አያንቀላፋም እግሮ
ቹ ደም ለማፍሰስ የፈጠኑ ናቸው አንደበቱም
ክፋውን ለመናገር፣ ያለ እሳት ከተማን
ያቃጥላል ነገሥታትንም እንደ አንበሳ ጩኸት
ያስጮህል የዋሁን እንደ አራስ ድብ አውሬ
ያደርገዋል እንደ በረሀ ዓሣማ ያደርገዋል
በሰይጣን ዘንድ ሞገስን አግኝቷልና ይህን ዋሸህ
ይህንንም ክፉ አደረግህ የሚለው የለም፡፡
ንጉሥም ስለርሱ እንደ አንበሳ ይጮሀል ባየውም
ጊዜ በርሱ ላይ ክፉ ለማድረግ አይቻለውም፡፡

፭ አሁንም የማርያም የደግነቷን ታላቅነት
መናገር እንደማይቻል የቢቱን የክፋቱን ነገር
ፈጽሞ መናገር አይቻለንም፣ አሁንም
የሃይማኖቱን ተግሣጽ እንናገር ጳውሎስም
ሁላችን በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት
እንመረመር ዘንድ አለን እንዳለ የሥራውን
ክፋት ስለመናገር አንመራመር፣ የቢቱ የትምህ
ርቱ ስንፋና ይህ ነው ወልድ ያለ አባቱ ይመ
ጣል አለ፡፡ አብን እንደ ንጉሥ ወልድንም እንደ
ሠራዊት አለቃ አደረገው፡፡ ንጉሥ ጠላቶቹን
እንዲበቀላቸው የሚወድዱትንም በጎ ዋጋ
እንዲሰጣቸው የሠራዊቱን አለቃ እንደሚልክ

ይትበቀሎሙ ለጸላእቱ ወከመ ይዕሥዮሙ ለእለ ያፈቅርዎ ወከማሁ ረሰየ ምጽአቶ ለወልድ፡፡አልቦ እንከ ዘሰማዕነ ዘከመዝ ዕልወተ ኢእምቅድመዝ ወኢእምድኅረዝ ኢእምኅበ አይሁድ ወኢእምኅበ ክርስቲያን ወኢእምኅበ ተንበላት፡፡አይሁድሰ ይብሉ እግዚአብሔር ወሀበ ሕገ ለሙሴ ወለእለ ኢዐቀቡ ትእዛዘ ኦሪት ይፈድዮሙ እግዚአብሔር አመ ዕለተ ደይን፡፡እስመ ይቤ ዳዊት ነቢዮሙ ወንጉሦሙ ምዕረ ነበበ እግዚብአብሔር ወዘንተ ከመ ሰማዕኩ፡፡እስመ ዘእግዚአብሔር ኀይል፡፡ወዚአከ እግዚኦ ኃይል፡እስመ አንተ ትፈድዮ ለኩሉ በከመ ምግባሩ፡፡ መዝ፷፩÷፲፪ ሮሜ፲፬÷፲

፩ ወበእንተዝ ይብሉ እግዚአብሔር ይፈድዮሙ ለኃጥአን ወይዔሥዮሙ ለጻድቃን፡ወለወልድሰ ይብልዎ ይመጽእ እምድኅረዝ፡፡ኢይብልዎ ወልደ እግዚአብሔር አላ ይብልዎ ወልደ ዳዊት እስመሀለዎሙ ይትወከፍዎ ለሐሳዌ መሲሕ፡፡ተንበላትሂ ይብሉ እግዚአብሔር ኢወለደ ወኢተወልደ፡፡ወለወልደ እግዚአብሔርሰ ይብልዎ በቃለ ገብርኤል ተፀነሰ እማርያም፡፡ይብልዎ ንባበ እግዚአብሔር ወኢይብልዎ ወልደ እግዚአብሔር፡፡ወምጽአቶሰ ለእግዚአብሔር ኢይክሕዱ፡፡ወካሕደ አይሁድሰ ወተንበላት በእንተ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመ ውእቱ ኢኮነ ወልደ እግዚአብሔር፡፡ ንሕነሰ ክርስቲያን ነአምን ከመ እግዚአብሔር ይመጽእ ምስለ ወልዱ ወመንፈሱ ቅዱስ፡፡በእንተ ምንትኬ ይትበሀል ኢይመጽእ አብ ዘበእንቲአሁ ይቤ ዳዊት እግዚብሔርሰ ገሀደ ይመጽእ አብ ዘበአንቲአሁ ይቤ በእንተ አብ ወአምላክነሂ ኢያረምም፡፡ይቤ በእንተ ወልድ አቅደመ ዜንዎ ምጽአቶ ለአብ ወአትለወ ከመ ኢያረምም ወልድ ወይትዋቀሦሙ ለሰቃልያን፡ በከመ ይቤ ዮሐንስ አቡቀለምሲስ ናሁ ይመጽእ በደመና ወትሬእዮ ኩላ ዓይን ወእልክቱኒ እለ ወግእዎ ይሬእይዎ ወይበክዩ በእንቲአሁ ኩሎሙ አሕዛበ ምድር፡፡እወ አማን አነ ውእቱ አልፋ ወኦ ይቤ እግዚአብሔር ዘሀሎ ወይሄሉ ወዘይመጽእ ዘውእቱ ይመልክ ኩሎ፡፡

፫ ለአይሁድሰ ይትዋቀሶሙ በእንተ ዘመነንዎ ወቀሰፍዎ በእንተ ዘሰቀልዎ ወረገዝዎ በከመ ይቤ መጽሐፍ ሀለዎሙ ይርአይዎ ለዘወግእዎ ገቦሁ፡፡ወለክርስቲያንሂ ይትዋቀሶሙ በእንተ ዘመነኑ እኅዋሆሙ እንዘ ይብል ርኅብኩ ወኢያብላዕክሙኒ፡፡ጸማዕኩ ወኢያስተይክሙኒ፡ነግደ ኮንኩ ወኢተወከፍክሙኒ

የወልድን አመጣጥ እንዲሁ አደረገ፣እንደዚህ ያለውን ክህደት ከዚህ በፊት ከዚህም በኋላ ከአይሁድ ዘንድ ከክርስቲያንም ዘንድ ከእስላሞችም ዘንድ አልሰማንም። አይሁድስ እግዚአብሔር ለሙሴ ሕግን ሰጠ የኦሪትንም ትእዛዝ ያልጠበቁትን በፍርድ ቀን እግዚአብሔር ዋጋቸውን ይከፍላቻዋል ይላሉ፡፡ነቢያቸውና ንጉሣቸው ዳዊት እግዚአብሔር ፈጽሞ ተናገረ እኔም ይህንን ሰማሁ ይቅርታ የእግዚአብሔር ነውና ኃይልም አቤቱ ያንተ ነውና አንተ ሁሉን እንደሥራው ትከፍለዋልህ ብሎ ተናግሯልና። መዝ፷፩÷፲፪ ሮሜ፲፬÷፲

፩ ስለዚህም ነገር እግዚአብሔር ኃጥአንን ይፈርድባቸዋል ጻድቃንንም በጎ ዋጋ ይሰጣቸዋል ይላል፡፡ወልድን ግን ከዚህ በኋላ ይመጣል ይሉታል የእግዚአብሔር ልጅም አይሉትም የዳዊት ልጅ ይሉታል ሐሳዌ መሲሕን ይቀበሉት ዘንድ አላቸውና፡፡እስላሞችም እግዚአብሔር አልወለደም አልተወለደምም ይላሉ፡ የእግዚአብሔርንም ልጅ በገብርኤል ቃል ከማርያም ተፀነሰ ይሉታል የእግዚአብሔር ንግግር ይሉታል የእግዚአብሔር ልጅ ግን አይሉትም የእግዚአብሔርን መምጣት ግን አይክዱም የአይሁድና የእስላሞች ክህደት ስለኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ አይደለም በማለት ነው፡ እኛ ግን ክርስቲያን ነን እግዚአብሔር ከልጁና ከቅዱስ መንፈሱ ጋር እንደሚመጣ እና ምናለን ዳዊት ስለርሱ የተናገረለት አብ ስለምን አይመጣም እግዚአብሔር በግልጥ ይመጣል ብሎ ስለአብ ተናገረ አምላካችንም ዝም አይልም ብሎ ስለወልድ ተናገረ፡ስለአብ መምጣት መናገርን አስቀደመ ወልድም ዝም እንደማይል ሰቃዮቹንም እንደሚወቅሳቸው አያይዞ ተናገረ፡፡ዮሐንስ አቡቀለምሊስ እነሆ በደመና ይመጣል ዓይንም ሁሉ ታየዋለች የወጉትም እነርሱ ያዩታል ስለርሱም የምድር አሕዛብ ሁላቸው ያለቅሳሉ አምን በእውነት መጀመሪያውና መጨረሻው አልፋና ኦሜጋ እኔ ነኝ ያለና የሚኖር የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ እግዚአብሔር አለ፡፡ መዝ፵፱÷፩ ራእ፩÷፯

፫ አይሁድን ስለናቁትና ስለገረፉት ስለሰቀሉትና መጽሐፍ ጐኑን የወጉትም ያዩት ዘንድ አላቸው እንዳለ ስለወጉት ነው፡፡ክርስቲያን የሆኑትንም ወንድሞቻቸውን ስለናቁ ተርቤ አላበላችሁኝም ተጠምቼ አላጠጣችሁኝም፣ እንግዳም ሆኜ አልተቀበላችሁኝም፣ ታረዝሁ አላለበሳችሁኝም፣ታምሜ አልጐበኛችሁኝም ታሥሬ ወደ እኔ መጥታችሁ አልጐበኛችሁኝም፣ ብሎ ይወቅሳቸዋል። እነርሱ አቤቱ መቼ ተርበህ

ዐረቁ ወኢያልበስክሙኒ ደወይኩ ወኢሐወጽ
ክሙኒ፡ተሞቃሕኩ ወኢመጻእክሙ ኀቤየ ወኢ
ነበብክሙኒ፡ወይቤልዎ እግዚኦ ማእዜኑ ርኢና
ከ ርኁበከ ወኢያብላዕናከ፡ወጽሙዐከኒ ወኢያ
ስተይናከ፡ነግደከሂ ወኢተወከፍናከ፡ዕሩቀከ ወ
ኢያልበስናከ፡ድውየከ ወኢሐወጽናከ፡ሙቁሐ
ከኒ ወኢመጻእነ ኀቤከ ወኢነበብናከ፡ወይቤሎ
ሙ ዘኢገበርክሙ ለ፩ እምእሉ ንዑሳን ሊተ ኢገበ
ርክሙ፡ሑሩ እምኔየ ርጉማን ውስተ እሳት ዘለዓ
ለም ዘድልው ለሰይጣን ወለመላእክቲሁ፡፡
ማቴ፳፭፥፴፩-፵፮

፳ አብሰ ኢይትዋቀሶሙ ለአይሁድ
እስመ ኢለብሰ ሥጋ በዘይትወከፍ ሕማማተ
እምኀበ ሰቃልያን፡ወባሕቱ ያገብእ ሎቱ ፍት
ሐ ለወልዱ ወይገንዩ ጸላዕቱ ታሕተ መከየደ
እገሪሁ፡በከመ ይቤ ዳዊት ይቤሎ እግዚእ ለእ
ግዚእየ ንበር በየማንየ እስከ አገብኦሙ ለጸላ
ዕትከ ታሕተ መከየደ እገሪከ፡አመ ዕርገቱ
ይቤሎ ንበር በየማንየ፡፡ወእምዝ ወሀቦ ዕድሜ
በእንተ ምጽአቱ ወይቤሎ እስከ አገብኦሙ ለጸ
ላዕትከ ታሕተ መከየደ እገሪከ ናሁኬ አየቀ
ቃለዝ መዝሙር በከመ ተለዐለ ወነበረ በየማነ
አቡሁ፡ካዕበመ ይመጽእ እንዘ ይነብር በየማ
ነ ወላዲሁ ወይገብኡ ጸላዕቱ ታሕተ መከየደ
እገሪሁ፡ኢይቤሎ አቡሁ ንበር ኀበ ካልዕ ገጸ
መካን እስከ አገብእ ለከ ፍርቃነ ወእትቤቀ
ሎሙ ለጸላዕትከ፡አላ ይቤሎ ንበር በየማንየ
እስከ አገብኦሙ ለጸላዕትከ ታሕተ መከየደ
እገሪከ፡፡ መዝ፻፱፥፩

፱ ዘልፈ ህልው አብ በጽርሐ አርያም
፡ወዘልፈ ህልው ወልድ በየማነ አቡሁ ፡ወአመ
ተለዐለ በሥጋዌሁ ነበረ ኀበ ዘትካት ህላዌሁ
ኢመንተወ በግጻዌ ኢተወሰከ በህላዌ፡ካዕበመ
ይመጽእ እንዘ ይነብር በየማነ ዘወለዶ በከመ
ይቤሎሙ ለሊቃነ ካህናት ትሬእይዎ ለወልደ
እጓለ እመሕያው እንዘ ይነብር በየማነ ኃይል
ወይመጽእ በደመና ሰማይ፡ናሁኬ ተዐውቀ
ዜና ምጽአቱ ለአብ ምስለ ወልዱ ዘይነብር በየ
ማኑ፡ኃይልሰ ይስመይ በእንተ ዘይገስስ ወዘኢ
ይትገሰስ በእንተ ዘይሬኢ ወዘኢያስተርኢ፡ አ
ሜሃ ይገብኡ ጸላዕቱ ለወልደ እግዚአብሔር
ታሕተ መከየደ እገሪሁ፡ በከመ ይቤ ጳውሎስ
ወኵሎ አልቦ ዘኀደገ ዘኢያግረረ ሎቱ ወል
ድኒ ይገኒ ለዘአግነየ ሎቱ፡፡ናሁኬ ዐውደ ም
ኵናን ዘአብ ወወልድ መወንፈስቅዱስ፡አብ
ይነብር ዐውደ በከመ ይቤ ሐዋርያ ወአመሰ
ለአብ ትጼውዕዎ ዘይኴንን እንዘገጸ ኢይነሥእ

አይተንህ አላበላንህም፤ ተጠምተህስ አላጠ
ጣንህም፤ መቼ እንግዳ ሆነህ አልተቀበልንህም፤
ታርዘህ አላለበስንህም፤ መቼ ታመህ አልጐበኘ
ንህም፤ ታሥረህስ ወዳንተ መጥተን አልጠ
የቅንህም፤ ይሉታል እርሱም ከነዚህ ከታናናሾቹ
ለአንዱ ያላደረጋችሁትን ለኔ አላደረጋችሁም
እናንተ ርጉማን ለሰይጣንና ለመላእክተኞቹ
ወደተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ሂዱ ይላቸዋል፡፡
ማቴ፳፭፥፴፩-፵፮

፳ አብ ግን አይሁድን አይወቅሳቸውም
ከሰቃዮች ዘንድ መከራን በሚቀበልበት ገንዘብ
ሥጋን አልለበሰምና ዳኙ ግን ፍርድን ለልጁ
ይሰጠዋል ጠላቶቹም ዳዊት ጌታ ጌታዬን
ጠላቶችህን ከእግሮችህ መረገጫ በታች
እስካስገዛልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ እንዳለው
ከእግሩ መረገጫ በታች ይገዛሉ፡፡ በሚያርግ
ጊዜም በቀኜ ተቀመጥ አለው፤ ከዚያም ስለ
መምጣቱ ጠላቶችህን ከእግሮችህ መረገጫ በታች
እስካስገዛልህ ድረስ ብሎ ጊዜ ሰጠው ፡፡እነሆ
የዚህ መዝሙር ቃል ከፍ ከፍ እንዳለ በአባቱም
ቀኝ እንደተቀመጠ አሳወቀ፡ ሁለተኛም በወላጁ
ቀኝ ተቀምጦ ይመጣል ጠላቶቹም ከእግሮቹ
መረገጫ በታች ይገዛሉ አባቱ ጠላቶችህን
ተበቅዬ ምስጋናን እስካመጣልህ ድረስ በሌላ
ሥፍራ ተቀመጥ አላለውም ጠላቶችህን ከእግ
ሮችህ በታች እስካስገዛልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ
አለው እንጂ፡፡ መዝ፻፱፥፩

፱ አብ ዘወትር በጽርሐ አርያም
ይኖራል ወልድም ዘወትር በአባቱ ቀኝ ይቀ
መጣል በለበሰውም ሥጋ ባረገ ጊዜ በቀደመ
አኗኗሩ ተቀመጠ በመልክ ሁለት አልሆነም
በባህርዩም አልተጨመረበትም የካህናት አለቆች
የሰውን ልጅ በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይ
ደመናም ሲመጣ ታዩታላችሁ እንዳላቸው በወ
ለደው ቀኝ ተቀምጦ ሁለተኛ ይመጣል፡፡እነሆ
በቀኙ ከሚቀመጥ ከልጁ ጋር የአብ የመምጣቱ
ዜና ታወቀ፤ ስለሚዳሰስ እርሱ ግን ስለማይዳሰስ
ስለሚያይ እርሱ ግን ስለማይታይ ኃይል ተባለ
ያን ጊዜም ጳውሎስ ሁሉን ከእግሮቹ መረገጫ
በታች አስገዛለት ሁሉን አስገዛለት ያላስገዛለት
የተወውም የለም እንዲህ የእግዚአብሔር ልጅ
ጠላቶቹ ከእግሮቹ በታች ይገዛሉ፡፡ ሁለተኛም
ሁሉ በተገዛለት ጊዜ ወልድም ላስገዛለት ይገዛል
አለ፡፡እነሆ የአብና የወልድ የመንፈስቅዱስም
አገዛዝ አንድ ነው አብ በአደባባይ ይገኛል ሐዋ
ርያው ፊት ሳያይ ለእያንዳንዱ እንደ የሥራው
የሚፈርድ አብን ብትጠሩት እንዳለ ወልድም
እርሱ ራሱ በወንጌል ፍርዱም እውነት ነው

በበምግባሩ ለለ፩፩ ወልድኒ ይኴንን በከመ
ይቤ ለሊሁ በወንጌል ወኲነኔየኒ ጽድቅ ውእቱ
፡፡ወመንፈስቅዱስ ይኴንን በከመ ይቤ ጳውሎ
ስ ወኢታአምሩኑ ከመ በመንፈስቅዱስ ንትሐ
ተት ኲልነ፡፡ ዮሐ፫÷፲፮ ፩ቆሮ፲፭÷፳፪

፲ ናሁኬ ፩ ምኩናን ዘመለኮተ
ሥላሴ፡፡ወበእንተሰ ዘይቤ ወልድ አብሰ ኢይ
ኴንን ወኢመነኒ አላ ኲሎ ኲነኔሁ አወፈዮ ለወ
ልዱ፡ዘንተሰ ይቤ በእንተቅሥት ዘይትዋቀሥሙ
ለአይሁድ ወለክርስቲያን፡፡ለአይሁድሰ በእንተ
ዘሰቀልዎ ወለክርስቲያንሂ፡፡በእንተ ዘመነኑ ቢ
ጸሙ በከመ ንቤ ቀዳሚ፡፡እስመ ለኲነኔ ወለቅ
ሥት ፪ ፍካሬሆሙ በከመ ይቤ ወንጌላዊ ውእ
ተ ዕለተ ተኳነኑ ሄሮድስ ወጲላጦስ እስመ
ጋእዝ ቦሙ እምቅድም፡፡ዘንተ ይቤ በእንተ
ኲነኔ ቅሥት፡፡ወለኲነኔ ሥቃይስ ካልዕ ፍካሬ
ሁ በከመ ይቤ እግዚእነ በወንጌል እስመ በኲ
ነኔ ዘኰነንክሙ ትትኴነኑ ወበመስፈርት ዘሰፈ
ርክሙ ይሰፍሩ ለክሙ፡፡ወቦ ኀበ ዘይቤ ወዘሰ
ይቤሎ ለእኁሁ ዘጸርቅ ረስሐ ውእቱ ይትኴነ
ን በዐውድ፡፡ወቦ ኀበ ዘይቤ እምቃልከ ትጸ
ድቅ ወእምቃልከ ትኴነን፡፡ ማቴ፳÷፳፪፣፯÷፮
ሉቃ፳፫÷፲፪

፲፩ ወቦ ዛልስኒ ፍካሬ ለብሂለ ኲነኔ
ወለብሂለ መኰንን፡፡ብሂለ መኰንንሰ እኃዜ
ዓለም ውእቱ ወብሂለ ኲነኔኒ ሥልጣነ መንግ
ሥቱ ውእቱ ዘዓለም፡፡በከመ ይቤ በመዝሙር
እስመ እግዚአብሔር መኰንን ውእቱ ዘንተ
የኀሥር ወዘንተ ያከብር፡፡ወካዕበ ይቤ እግዚአ
ብሔር መኰን ነጽድቅ፡፡ኃያል ወመስተዐግሥ
፡፡ወካዕበ ይቤ ተለዐለ ዘይኴንና ለዓለም፡፡ወበ
እንተ መኳንንተ ምድርኒ ይቤ ጳውሎስ ወዘሰ
አበየ ተኰንኖ ለመኰንን ትእዛዘ እግዚአብ
ሔር አበየ፡፡ትብል ቅድስት ኦሪት ለመኰንነ
ሕዝብከ ኢኪት ኢትበል፡ወካዕበመ ይቤ መኳ
ንንተ ኢትሕሚ፡፡ዘጸ፳፪÷፳፰መዝ፸፬÷፰ሮሜ፲፫÷፩

፲፪ ወበእንተ ወልደ እግዚአብሔርኒ ይቤ
በመዝሙር ኰንን በጽድቅ ነዳያነ ሕዝብከ፡
ወአድኅኖሙ ለደቂቀ ምስኪናኒከ:ወካዕበ ይቤ
ወይኴንን እምባሕር እስከ ባሕር፡ወእምአፍ
ላግ እስከ አጽናፈ ዓለም፡፡ወካዕበ ይቤ ወይኴ
ንና ለዓለም በጽድቅ፡ወለአሕዛብኒ በርትዕ፡፡
ናሁ አርአይኩክሙ በ፫ ፍና ብሂለ ተኰንኖ
ወብሂለ መኰንን ኀበ ሥልጣነ ሢመት ወብሂ
ለ ኲነኔ ኀበ ሥቃይ ወብሂለ ተኳንኖ ኀበ ቅስ
ት፡፡ መዝ ፸፩÷፪፣፰

እንዳለ ይፈርዳል፡፡ መንፈስቅዱስም ይፈርዳል
ጳውሎስ ሁላችን በመንፈስቅዱስ እንድን
መረመር አታውቁምን እንዳለ፡፡ ዮሐ፫÷፲፮
፩ቆሮ፲፭÷፳፪

፲ እነሆ የሥላሴ አገዛዝ መንግሥት
አንድ ነው፣ ወልድ አብ ግን በማንም ላይ ቢሆን
አይፈርድም ፍርድን ሁሉ ለልጁ ሰጠው
ስላለው ግን ይህንንስ አይሁድንና ክርስቲያንን
ስለ ሚወቅስበት የወቀሳ ፍርድ ተናገረ አይ
ሁድን ስለሰቀሉት ክርስቲያንንም አስቀድመን
እንደተናገርን ባልንጀሮቻቸውን ስለናቁ ነው
የፍርድና የወቀሳ ትርጉም ወንጌላዊ እንደተናገረ
ሁለት ወገን ነው፡፡በዚያም ቀን ሄሮድስና ጲላጦ
ስ ተነጋገሩ ከፊት ጀምሮ ጠብ ነበራቸውና ይህን
ስለ ወቀሳ ፍርድ ተናገረ፣ የሥቃይ ፍርድ ግን
ትርጉሙ ሌላ ነው ጌታችን በወንጌል በፈረዳች
ሁት ፍርድ ይፈረድባችኋል በሠፈራችሁበትም
መሥፈሪያ ይሠፈርባችኋል እንዳይፈረድባችሁ
አትፍረዱ የሚልም አለ፡፡ ወንድሙንም ጉድፍ
ጨርቃም ያለ እርሱ በአደባባይ ይፈረድበታል
የሚልም አለ ፡፡ከቃልህ የተነሣ ትጸድቃለህ
ከቃልህም የተነሣ ይፈረድብሀል የሚልም አለ፡፡
ማቴ፳÷፳፪፣፯÷፮ ሉቃ፳፫÷፲፪

፲፩ ሦስተኛም ኲነኔና መኰንን ለማለት
ትርጉም አለው መኰንን ማለት ዓለምን የያዘ
ማለት ነው ኲነኔም ማለት ዘላለማዊ
የመንግሥቱ ሥልጣን ነው በመዝሙር እግዚአ
ብሔር ፈራጅ ነው ይህን ያዋርዳል ይህንንም
ያከብራል እንዳለ፡፡ሁለተኛም እግዚአብሔር
ኃያልና ታጋሽ በጽድቅም ፈራጅ ነው አለ፡፡ ዳግ
መኛም ዓለምን የሚገዛ ከፍ ከፍ አለ
ይላል፡፡ስለምድር ገዢዎችም ጳውሎስ ለገዢ
አልገዛም ያለ ለእግዚአብሔር ትእዛዝ አይገዛም
ይላል፣ የከበረች ኦሪትም በወገኖችህ አስተዳደሪ
ላይ ክፉውን አትናገር አለች ሁለተኛም
አስተዳዳሪዎችን አትማ አለ፡፡ ዘጸ፳፪÷፳፰
መዝ፸፬÷፰ ሮሜ፲፫÷፩

፲፪ ስለ እግዚአብሔር ልጅም
በመዝሙር የተቸገሩ ወገኖችህን በጽድቅ ግዛ
የችግረኞችንም ልጆች አድናቸው ይላል፡፡ዳግመኛ
ም ከባሕር ዳርቻ እስከ ባሕር ዳርቻ ከወንዞችም
እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ ይገዛል አለ፡፡ ሁለተኛም
ዓለምን በጽድቅ አሕዛብንም በፍርድ ይዳኛል
አለ፡፡እነሆ በሦስት መንገድ አሳየሁአችሁ መገ
ዛትና ገዥ ማለት ለሹመት ሥልጣን ማለት
ለሥቃይ መፈራረድ ማለት ነው፡፡ መዝ
፸፩÷፪፣፰

፲፫ ወዘይቤሰ አብሰ ኢይኴንን
ወኢ መነሂ አላ ኩሎ ኩነኔሁ አወፈዮ ለወልዱ
ኩነኔ ቅሥት ውእቱ፡፡ወበእንተሰ ምጽአተ አብ
ይቤ ዳንኤል ወአምጽኡ መናብርተ ለብሉየ
መዋዕል ወሥዕርተ ርእሱ ጸዓዳ ከመ ፀምር
ወአዕይንቲሁ ከመ ነደ እሳት ወፈለገ እሳት
ይውኅዝ ቅድሜሁ፡ወአምጽኡ መጻሕፍተ ወከ
ሡትዋ በቅድመ እግዚአብሔር፡ወለመጽሐፈ
ሕይወትሰ ከሡትዋ እንተ ባሕቲታ፡፡ወመጽአ
ወልደ እጓለእመሕያው ወነበረ ኀበ ብሉየ መዋ
ዕል፡ ወተውህበ ሎቱ ምኩናን ዘለዓለመ ዓለም
:ወመንግሥቱሂ መንግሥት ዘኢየኀልቅ፡፡ ናን
ቅሀኬ ልበነ ለፍካሬ ዝንቱ ትንቢት ወአምጽ
ኡ መናብርተ ለብሉየ መዋዕል ዘይቤ በእንተ
ዐውደ ምኩናን ዘምጽአተ አብ፡፡ወፈለገ እሳት
ይውኅዝ ቅድሜሁ ዘይቤ ቃላየ ደይናሙ ለኃ
ጥአን ዘይውኅዝ ቅድሜሁ ለዘይፈድዮሙ በቀ
ለ ከመ ርእዮሙ ይፍርሀ ወነጺሮሙ ይብክ
ዩ፡፡አሜሃ ይከውን ንሰሓ ዘኢይበቍዕ ወብካይ
ዘኢያድኅን እስመ ኢነስሑ በሕይወቶሙ፡፡
ዳን፯፥፱ ዮሐ፭፥፳፭

፲፬ ወአምጽኡ መጽሐፈ ወከሡትዋ
በቅድመ እግዚአብሔር ዘይቤ መጽሐፈ ዕዳ
ሆሙ ለኃጥአን ዘገበርዎ በዝየ ይትረከብ በህየ
፡፡ ወዘገብርዎ በክቡት ይትነበብ በክሡት፡፡
ወአልቦ ዘይክል ሠውሮ ኃጣውኢሁ አሜሃ እስ
መ መጽሐፈ ጌጋይ ትዛለፎ፡፡ለመጽሐፈ ሕይ
ወትሰ ከሡትዋ እንተ ባሕቲታ ዘይቤ መጽሐ
ፈ ጻማሆሙ ለቅዱሳን ልዑል ወሥነ ምግባሮ
ሙ ዘልክዕት ውስተ መጽሐፈ ሕይወት፡፡ወተ
ከሥቶታሰ ለመጽሐፈ ሕይወት እንተ ባሕቲ
ታ እስመ አኮ ዘትዴመር መጽሐፈ ገድሎሙ
ለጻድቃን ምስለ መጽሐፈ ዕዳሆሙ ለኃጥአ
ን፡፡ ለኃጥአንሰ ምቅዋሞሙ መንገለ ጸጋም፡፡
ወለጻድቃንኒ ምቅዋሞሙ መንገለ የማን ወመ
ጽሐፈ ሕይወቶሙኒ እንተ ትዌድሶሙ መንገ
ለ የማን፡እስመ ዕሤቱ ለሰብእ ምስሌሁ ወም
ግባሩ ቅድመ ገጹ፡፡ወመጽአ ወልደ እጓለእመ
ሕያው ወነበረ ኀበ ብሉየ መዋዕል ዘይቤ ናሁ
ኬ ነገረ ምጽአተ ወልድ ወነቢረ ኀበ አቡሁ፡፡
ወበዝኒ ኢትሌቡኑ፡፡ናሁኬ ነቢረ አብ ወወል
ድ ውስተ ፩ ዐውድ ወአሐቲ ሙቃስ ዘይከው
ን በማሕተተ መንፈስቅዱስ፡በከመይቤ እግዚ
እነ በወንጌል ወመጺኦ ውእቱ ጳራቅሊጦስ ይዛ
ለፍ ለዓለም በእንተ ጽድቅ ወበእንተ ኃጢአ
ት፡፡በእንተ ጽድቅሰ እስመ ተኰነነ መልአኩ

፲፫ አብስ በማንም ላይ አይፈ
ርድም ፍርድን ሁሉ ለልጁ ሰጠው እንጂ ያለው
የወቀሳ ፍርድ ነው፡፡ ስለ አብ መምጣት ግን
ዳንኤል በዘመን ለሸመገለውም ዙፋን አመጡለት
የራሱም ጠጉር እንደ ግምጃ ነው ዓይኖቹም
እንደ እሳት ነበልባል ናቸው የእሳትም ወንዝ
በፊቱ ይፈሳል፤ መጽሐፍ አመጡ በእግዚ
አብሔርም ፊት ገለጡአት የሕይወትን መጽሐ
ፍንም ብቻዋን ገለጡአት የሰው ልጅም መጥቶ
በዘመን በሸመገለው ዘንድ ተቀመጠ የዘላለምም
መንግሥት ተሰጠው መንግሥቱም ፍጻሜ
የሌለው መንግሥት ነው አለ፡፡ለዚህ ትንቢት
ትርጉም ልባችንን እናንቃ በዘመን ለሸመገለው
ዙፋን አመጡለት ያለው ስለ አብ መምጣት
የፍርድ አደባባይ ነው፡፡ የእሳት ወንዝ በፊቱ
ይፈስሳል ያለው፡ በብድራት በሚፈርድባቸው
ፊት ነው አይተው እንዲፈሩ ተመልክተውም
እንዲያለቅሱ የሚፈስስ የኃጥአን ፍርዳቸው
ነው፡ ያን ጊዜ የማይጠቅም ንስሓ የማያድንም
ልቅሶ ይሆናል በሕይወታቸው ንስሓ አልገ
ቡምና፡፡ ዳን፯፥፱ ዮሐ፭፥፳፭

፲፬ መጽሐፍም አምጥተው በእግዚአብሔር
ፊት ገለጡአት ያለው የኃጥአን የዕዳቸው
መጽሐፍ ነው በዚህ ዓለም የሠሩት በዚያ ይገኛ
ል በሥውርም የሠሩት በግልጥ ይነበባል፡፡ ያን
ጊዜ ኃጢአቱን መሸሸግ የሚችል የለም የበደል
መጽሐፍ ትከራ ከራዋለችና የሕይወት መጽሐ
ፍንም ብቻዋን ገለጡአት ያለው የልዑል ቅዱሳን
የድካማቸው መጽሐፍ ነው፡፡ በጎ ሥራቸው
በሕይወት መጽሐፍ የተጻፈች ናት የሕይወት
መጽሐፍ ብቻዋን መገለጧ የጻድቃን የገድላቸው
መጽሐፍ ከኃጥአን የዕዳቸው መጽሐፍ ጋር
አትደመርምና የኃጥአን መቆሚያቸው በስተግራ
ነው የምትዘልፋቸውም የዕዳቸውም መጽሐፍ
በግራ በኩል ናት፡፡ ጻድቃንም መቆሚያቸው
በስተቀኝ ነው የምታወድሳቸውም የሕይወት
መጽሐፍ በስተቀኝ ናት፤ለሰው የሚሰጠው በጎ
ዋጋ ከእርሱ ጋር ሥራውም በፊቱ የተገለጠ
ነውና፡፡ የሰው ልጅም መጥቶ በዘመን በሸመ
ገለው ዘንድ ተቀመጠ ያለው እነሆ የወልድን
መምጣትና በአባቱ ቀኝ በኩል የመቀመጡን
ነገር ተናገረ፡፡ በዚህም አታስተውልምን፤የአብና
የወልድ በአንድ አደባባይ መቀመጥ እነሆ!
በመንፈስቅዱስ መመርመር የሚሆን ወቀሳም
አንዲት ናት፡ ጌታችን በወንጌል አጽናኙም
መጥቶ ዓለምን ስለጽድቅና ስለ ኃጢአት
ይፋረደዋል ስለ ጽድቅ አላመ ኑብኝምና ስለ
ኃጢአትም የዚህ ዓለም ገዢ ተፈርዶበታልና፡፡
አንተ ዝንጉ ዛሬም እስከ መቼም

ለዝ ዓለም፡፡አእምርኬ ኦ ረሲዕ ከመ ኢይትፈለጥ ጽምረተ ሥላሴ እምይእዜኒ ወእስከ ማእዜኒ፡፡ ዮሐ፲፯÷፳

፲፭ ወአመ ትስብእተ መለኮቱ ለወልድ ይቤላ ገብርኤል ለማርያም በእንተ መንፈስቅዱስ፡ መንፈስቅዱስ ይመጽእ ላዕሌኪ፡ወበእንተ አብኒ ይቤ ወኃይለ ልዑል ይጼልለኪ፡ወበእንተ ወልድኒ ይቤ ወዘኒ ይትወለድ እምኔኪ ቅዱስ ውእቱ ወይሰመይ ወልደ ልዑል፡፡ናሁኬ ሥላሴ ኀበ ዝኒ፡፡ወበውስተ ዮርዳኖስኒ እንዘ ይጠመቅ ወልድ ስምዐ ኮነ አብ እንዘ ይብል ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር ወነበረ ዲቤሁ መንፈስ ቅዱስ በርእየተ ርግብ፡፡ናሁኬ ሥላሴ ኀበ ዝኒ፡፡ ማቴ፫÷፲፮ ሉቃ፫÷፳፪

፲፮ ወካዕበመ ይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ለአርዳኢሁ ሑሩ ወስብኩ ውስተ ኩሉ አጽናፈ ዓለም ወእንዘ ታጠምቅዎሙ በሉ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ፡፡ አዘዘ ተጠምቆ በዘኢይትሌለይ ሥላሴ፡ አማኀፀኑነ ኀበ ሥላሴ ዘአጥመቁነ ወዘሂ መሀሩነ አዕቀቡነ ስመ ሥላሴ እመሰ ተጠመቅነ በስመ ሥላሴ ነአምር ከመ በዐውደ ሥላሴ ንትሐተት፡፡ይቤ ለሊሁ እንዘ ይትዋቀሶሙ ለአይሁድ አኮ አነ ዘአስተዋድየክሙ ኀበ አብ: ሀሎ ሙሴ ዘያስተዋድየክሙ ዘኪያሁ ትሴፈዉ፡፡እመሰኬ ኢይመጽእ አብ ምስለ ወልዱ በእፎኬ ይክል ሙሴ አስተዋ ድዮቶሙ ለሕዝቡ ኀበ አብ በእንተ ዘኢአምኑ በወልደ እግዚአብሔር ኀበ ኢሀሎ አብ፡፡ለእመ አልቦ ምጽአተ አብ አልቦ አስተዋድዮቱ ለሙሴ፡፡ ለእመ አልቦ አስተዋድዮቱ ለሙሴ፡፡አልቦ ዘለፋ አይሁድ፡፡ወለእመ አልቦ ዘለፋ አይሁድ ሕስወ ረሰይክምዎ ለዘአይት ሔሰው ቃለ እግዚአብሔር፡፡ ማቴ፳፰÷፲፱ ዮሐ፭÷፵፭

፲፯ ወካዕበ ይቤ እግዚእነ በወንጌል ዘሰ አምነኒ በገጸ ሰብእ አአምኖ አነኒ በገጸ አቡየ ዘበሰማያት፡፡ወዘሰ ክሕደኒ በገጸ ሰብእ እክሕዶ አነኒ በገጸ አቡየ ዘበሰማያት፡፡ናሁኬ ተግህደ ምጽአተ አብ በአፈ ወልዱ፡፡ እመሰ ኢሀሎ ምጽአተ አብ እምኢይቤ ለዘአምነኒ በገጸ ሰብእ አአምኖ በገጸ አቡየ፡፡ወለዘክሕደኒ በገጸ ሰብእ እክሕዶ በገጸ አቡየ ዘበሰማያት፡፡ ናሁኬ አስተርአየ ወአስተናጸረ ወልደ እግዚአብሔር በገጸ አቡሁ ምስለ ገጸ ዘየአምን ቦቱ በገጸ ሰብእ እንዘ የአምኖ በገጸ አብ ዘበሰማያት፡፡ወለዘሂ ክሕዶ በገጸ ሰብእ እንዘ ይክሕዶ በገጸ አቡሁ ዘበሰማያት:: ወበእንተዝ ቃል አጥብዑ ሰማዕት ለሰዊነ ስምዕ እንዘ ይትዔገሡ መጥባሕተ ወእሳተ ከመኢይክሕዶሙ በገጸ አቡሁ

መች የሥላሴ አንድነት እንደማይለይ ዕወቅ:: ዮሐ፲፯÷፳

፲፭ የወልድ መለኮት ሰው በሆነ ጊዜ ገብርኤል ስለ መንፈስቅዱስ ማርያምን መንፈስቅዱስ ባንቺ ላይ ይመጣል ብሎ ነግሯታል፡፡ ስለ አብም የልዑል ኃይል ይጋርድሻል አላት ስለ ወልድም ካንቺም የሚወለደው ቅዱስ ነው የልዑል ልጅም ይባላል እነሆ ሥላሴ በዚህ አሉ በዮርዳኖስም ወልድ ሲጠመቅ አብ የምወደው ልጄ ይህ ነው ብሎ መሰከረ መንፈስቅዱስም በርግብ አምሳል በራሱ ላይ ተቀመጠ እነሆ በዚህም ሥላሴ አሉ:: ማቴ፫÷፲፮ ሉቃ፫÷፳፪

፲፮ ሁለተኛም ጌታ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ሂዱና በዓለም ዳርቻዎች ሁሉ አስተምሩ ስታጠምቁአቸውም በአብና በወልድ በመንፈስቅዱስ ስም በሉ ብሎ በማይለይ ሥላሴ መጠመቅን አዘዘ::ያጠመቁን በሥላሴ ዘንድ አደራ ሰጠን ያስተማሩንም የሥላሴን ስም አስያዙን በሥላሴ ስም ከተጠመቅንስ በሥላሴ አደባባይ እንደምንመረመር እናውቃለን እርሱ ራሱ አይሁድን ሲወቅሳቸው ወደ አብ የምከሳችሁ እኔ አይደለሁም የሚከሳችሁ ተስፋ የምታደርጉት ሙሴ አለ ብሎ ተናገረ:: አብ ከልጁ ጋር ካልመጣ ሙሴ በእግዚአብሔር ልጅ ስላላመኑ አብ በሌለበት ወገኖቹን ወደ አብ ይከሳቸው ዘንድ እንደምን ይቻለዋል፣ የአብ መምጣት ከሌለ የሙሴም መካሰስ የለም የሙሴም መካሰስ ከሌለ የአይሁድ መወቀስ የለም የአይሁድ መወቀስ ከሌለ የማይታበለውን የእግዚአብሔርን ቃል ሐሰት አደረጋችሁት:: ማቴ፳፰÷፲፱ ዮሐ፭÷፵፭

፲፯ ዳግመኛም ጌታችን በወንጌል በሰው ፊት ያመነብኝን እኔም በሰማያት ባለ በአባቴ ፊት አምነዋለሁ አለ፡ በሰው ፊት የካደኝን እኔም በሰማያት ባለ አባቴ ፊት እክደዋለሁ አለ:: እነሆ የአብ መምጣቱ በልጁ አንደበት ተገለጠ የአብ መምጣት ባይኖር በሰው ፊት ያመነብኝን እኔም በአባቴ ፊት አምነዋለሁ ብሎ በሰው ፊት የካደኝን በሰማያት ባለ በአባቴ ፊት እክደዋለሁ ባላለ ነበር:: እነሆ የእግዚአብሔር ልጅ በሰው ፊት የሚያምንበትን በሰማያት ባለ በአብ ፊት ሲያምነው በሰው ፊት የካደውንም በሰማያት ባለ በአባቱ ፊት ሲክደው የአባቱን ፊት ከሰው ፊት ጋር አስተያየ አነጻጸረ :: ስለዚህም ቃል በሰማያት ባለ በአባቱ ፊት እንዳይክዳቸው

ዘበሰማያት፡ወዕዝራኒ ተስእሎ ወይቤሎ ብቍዕኒ እግዚእየ እመ ረከብኩ ሞገሰ ቅድመ አዕይንቲከ ንግሮ ለገብርከ በመኑ ትሔውጽ ዓለመከ ፡፡ወይቤሎ ቀዳሚሁሰ በወልደ እጓለ እመሕያው ወደኃሪሁሰ ለልየ፡፡ወዘይቤሰ ነቢይ በመኑ ትሔውጽ ዓለመከ እንዘ ይፌቅድ ማሕሠሠ በእንተ ምጽአተ እግዚአብሔር ውስተ ዓለም ወዘይቤሎሰ እግዚአብሔር ቀዳሚሁሰ በወልደ እጓለ እመሕያው በእንተ ምጽአተ ወልዱ ኅበ ተሠግዎ፡፡ እስመ ወልደ እጓለ እመሕያው ይሰመይ ወልደ እግዚአብሔር በከመ ይቤ ለሊሁ እስመ ወልደ እግዚአብሔር ወልደ እጓለእመሕያው ውእቱ፡፡ወካዕበመ ይቤ እስመ ኢመጽአ ወልደ እጓለ እመሕያው ከመ ይትለአክዎ ዘእንበለ ዳእሙ ከመ ይትለአክ፡፡ወዓዲ ይቤ እስመ ኢመጽአ ወልደ እጓለ እመሕያው ከመ ይኰንኖ ለዓለም ዘእንበለ ዳእሙ ከመ ያሕይዎ ለዓለም፡፡ሉቃ፳፪፥፷፱ ማቴ፳፮፥፷፬ ማር፲፬፥፷፪

፲፰ ወዓዲ ይቤ ትሬእይዎ ለወልደ እጓለ እመሕያው እንዘ ይነብር በየማነ ኃይል ወይመጽእ በደመና ሰማይ፡፡ዳንኤልኒ ይቤ ወመጽአ ወልደ እጓለ እመሕያው ወነበረ ኅበ ብሉየ መዋዕል፡፡ናሁኬ ኩሎን መጻሕፍት ይሰምያሁ ወልደ እጓለ እመሕያው ለወልደ እግዚአብሔር፡፡ወለአብሰ ኢይሰምያሁ ወልደ እጓለ እመሕያው እስመ ኢለብሰ ሥጋሁ ለእጓለእመሕያው፡፡ወበእንተዝ ይቤሎ ለዕ ዝራ ቀዳሚሁሰ በወልደ እጓለ እመሕያው፡፡ ዘንተ ይቤ በእንተ ምጽአተ ወልዱ፡፡ ወደኃሪሁሰ ለልየ ይቤ በእንተ ምጽአተ ዚአሁ፡፡ናሁኬ ተረክበ ጥንቁቀ ፍናምጽአቱ ለአብ፡፡ጳውሎስኒ ይቤ ቀዳሚ ክርስቶስ ይእዜኒ ክርስቶስ አመ በምጽአቱ፡፡ወማኅለቅቱሰ አመ ተወፈየ እግዚአብሔር መንግሥቶ አብ ወአመ ተሥዕረ ኩሉ ምኲናን፡፡ወካዕበመ ነገረ ዮሐንስ አቡቀለምሲስ በእንተ ምጽአተ አብ ወወልድ ወይቤ ወእምዝ ርኢኩ ሰማየ ሐዲሰ ወምድረ ሐዳሰ፡እስመ ሰሰለ ሰማይ ቀዳማዊ ወምድርኒ ቀዳማዊት ወባሕርኒ ተሥዕረት እንከ፡፡ወለሀገርኒ ቅድስት ሐዳስ ኢየሩሳሌም ርኢክዋ ወረደት እምሰማይ እምኅበ እግዚአብሔር ድሉት ይእቲ ከመ መርዓት ሥርጉት ለምታ፡፡ ወሰማዕኩ ቃለ ዐቢየ እምሰማይ ዘይብል ናሁ ቅድስቱ ለእግዚአብሔር ምስለ እጓለ እመሕያው ኅደረት ምስሌሆሙ፡፡ወእሙንቱኒ ይከውንዎ ሕዝቦ ወውእቱኒ ይከውኖሙ አምላኮሙ ወይሄሉ እግዚአብሔር ምስሌሆሙ ወያሴስል አንብዐ እም አዕይንቲሆሙ፡፡ወአልቦ እንከ እስመ ኀለፈ

ሰማዕታት ስለቱንና እሳቱን ታግሰው ምስክር ለመሆን ጩኸኑ፡፡ ዕዝራም ጌታዬ ሆይ አቤቱ በዓይኖችህ ፊት ባለሟልነትን አግኝቼ ከሆነ ዓለምህን በማን እንደ ምትጐበኝ ለባሪያህ ንገረው ብሎ ጠየቀው፤እርሱም የመጀመሪያውን ባለው ልጅ ኋለኛውን ግን እኔ ራሴ እጐበኘዋለሁ አለው፡፡ ነቢዩ ዓለምህን በማን ትጐበኘዋለህ ያለው ስለ እግዚአብሔር ወደ ዓለም መምጣት መመርመርን ሽቶ ነው፡፡ እግዚአብሔርም መጀመሪያ በሰው ልጅ ያለው የልጁን ሰው ለመሆን መምጣት ነው እርሱ ራሱ የእግዚአብሔር ልጅ የሰው ልጅ ነውና እንዳለ የሰው ልጅ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላልና፡፡ ሁለተኛም የሰው ልጅ ሊያገለግል እንጂ ያገለግሉት ዘንድ አልመጣምና አለ፡፡ ከእንደገናም የሰው ልጅ ዓለምን ሊያድነው እንጂ ሊፈርድበት አልመጣምና አለ፡፡ ሉቃ፳፪፥፷፱ ማቴ፳፮፥፷፬ ማር፲፬፥፷፪

፲፰ ዳግመኛም የሰውን ልጅ በኃይል ቀኝ ተቀምጦ በሰማይ ደመና ሲመጣ ታዩታላችሁ አለ፡፡ ዳንኤልም የሰው ልጅም መጥቶ በዘመን በሸመገለው ዘንድ ተቀመጠ አለ፡፡እነሆ መጻሕፍት ሁላቸው የእግዚአብሔርን ልጅ የሰው ልጅ ይሉታል፡፡አብን ግን የሰው ልጅ አይሉትም የሰውን ልጅ ሥጋ አለበሰምና፡ ስለዚህም ዕዝራን መጀመሪያ በሰው ልጅ አለው ይህን ስለ ልጁ መምጣት ተናገረ፡፡ ኋለኛውን እኔ ራሴ አለ ስለራሱ መምጣት፤ እነሆ የአብ የመምጣት ነገር በጉላ በተረዳ ነገር ታወቀ፡፡ ጳውሎስ ትናንት ክርስቶስ ነው ዛሬም ክርስቶስ፤ በመምጣቱ ጊዜ በመጨረሻው እግዚአብሔር መንግሥትን ከአብ በተቀበለ ጊዜ ግዛትም ሁሉ በተሻረ ጊዜ ነው አለ፡፡ ሁለተኛም ዮሐንስ አቡቀለምሲስ ስለ አብና ስለ ወልድ መምጣት እንዲህ ብሎ ተናገረ ከዚህም በኋላ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር አየሁ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱም ምድር አልፈዋልና፡፡ ባሕርም ከእንግዲህ ተሽራለች ቅድስት ሀገር አዲስቷ ኢየሩሳሌምንም ለባሏ እንደ ተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁአት፡፡ ከሰማይም እነሆ የእግዚአብሔር ቅድስት ከሰው ልጅ ጋር በነርሱ ዘንድ አደረች እነርሱም ወገኖቹ ይሆኑታል እርሱም አምላካቸው ይሆናል እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ይኖራል ከዓይኖቻቸውም እንባን ያብሳል ከእ ንግዲህ ሞትና ዋይታ ልቅሶና መከራ የለም ከእንግዲህ ወዲያ የቀደመው ሥርዓት አልፏልና የሚል ድምፅ ሰማሁ በዙፋኑም የተቀመጠው እነሆ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ አለ፡፡ እኔንም ይህ ቃል በእውነት የተነገረ የሚሆንም ነውና ጻፍ

www.ethiopianorthodox.org

ዘቀዳሚ ሥርዓት ወይቤ ዘይነብር ዲበ መንበሩ ናሁ እገብር ኩሎ ሐዲሰ፡፡ወይቤለኒ ጸሐፍ እስመ ዝንቱ ቃል እሙን ዘበጽድቅ ውእቱ ዘይከውን ፡እስመ አነ ውእቱ አልፋ ወኦ ወአነ ቀዳማዊ ወደ ኃራዊ፡፡ ወአንሰ ለዘጸምአ እሁቦ ይሰተይ እምነቅዐ ሕይወት በከንቱ፡፡ ወዘሰ ሞአ ይወርሶ ለዝንቱ ወእ ከውኖ አምላኮ ወውእቱኒ ይከውነኒ ውሉድየ፡፡ ወእለሰ ይፈርህዎ እንዘ የአምኑ ወያጌምኑ ርኩሶሙ ወይቀትሉ ወይዜ ምዉ ወይገብሩ ሥራየ ወያመልኩ አማልክተ ወኩሎ ሐሰተ ይከውኖሙ ምንዳቤሆሙ ገሃነም ዘእሳት ወተይ ወዝንቱ ዳግም ሞት፡፡ ዳን፲፪÷፱

፲፱ መጽአ ፩ እምነ እልኩቱ መላእክት እለ ይጸውሩ ፯ ጽዋዓተ እለ ምሉአን ፯ መቅሠፍታተ ደኃርያተ፡፡ ወተናገረ ምስሌየ ወይቤ ለኒ ነዓ አርእይከሃ ለመርዓት ለብእሲተ በግዑ፡፡ወወሰደኒ መንፈስ ውስተ ደብር ዐቢይ ወነዋኅ ወአርአየኒሃ ለሀገር ቅድስት ኢየሩሳሌም እንተ ትወርድ እምሰማይ እምኀበ እግዚአብሔር ወስብሐተ እግዚአብሔር ላዕሌሃ: ወከዋክብቲሃኒ ይመስሉ ከመ ዕንቍ ክቡር ወጽዕዱት ከመ ባሕርይ ወዐቢይ አረፍታ ወነዋኅ ጥቅማ ፡፡ወባቲ ፲ወ፪ አናቅጽ ወውስተ ፲ወ፪ አናቅጽ ፲ወ፪ መላእክት፡፡ወጽሑፍ አስማተ ፲ወ፪ ሕዝበ እስራኤል:ውስተ አንቀጸ ጽባሐውያን ፫ ወውስተ አንቀጸ ዐረባውያን ፫፡፡፲ወ፪ መሠረታቲሃ ለአረፍተ ሀገራ ወጽሑፍ ውስቴቶን አስማተ ፲ወ፪ ሐዋርያተ በግዑ፡፡ወዝክቱኒ ዘይትናገር ምስሌየ ይጸውር ሕለተ አምጣነ በዘ ቦቱ ይሜጥና ለይእቲ ሀገር ወለአናቅጺሃ ወለአረፍቲሃ፡፡ወርብዕት ይእቲ ሀገር በአምጣነ ኑኃ ወግድማ፡፡ወመጠና ለይእቲ ሀገር በውእቱ ሕለት ወኮነ አምጣኒሃ ፲ወ፪፻ ኑኃ ወግድማ ወቆማኒ ዕሩይ፡፡ወእምዝ መጠነ አረፍቲሃ ፻፵ወ፬ በእመተ ሰብእ ፩ በእመተ መልአክ::

፳ ወውስተ ርእሰ አረፍቲሃ ለይእቲ ሀገር በዕንቈ ኢያስጲድ ወትመስል ሀገራ ከመ ዘበ ወርቅ ንጹሕ ግብረታ፡፡ወመሠረተ አረፍተ ሀገራ ከመ ማህው ጸዓዳ ዘሥርግው በኩሉ ዕንቍ ክቡር፡፡ወቀዳማዊት መሠረት ዘኢያስጲድ፡፡ ወካልዕት በሰንፔር ፡ወሣልሲት በኬልቄዶን፡፡ ወራብዕት በዘመረግድ፡፡ወኃምስት በሰርዶንክስ:: ወሳድሲት በሰርዴዮን፡፡ ወሳብዕት በክርስቲሎቤ ወሳምንት በቢረሌ፡፡ወታስዕት በወራውሬ:: ወዓሥርት በክርስጵስስ፡፡ወእንተ ዐሥሩ ወአሐቲ በያክንት ወእንተ ዐሥሩ ወክልዔ በአሜትስጢስ፡፡ ወዴዴያቲሃኒ ፲ወ፪ በዐሥሩ ወክልዔ ባሕርይ ለለ፩ ዴዴ አሐቲ ባሕርይ፡፡ወጽጕ ሀገራ ከመ ወርቅ

እኔ አልፋ እና ኦሜጋ ነኝ እኔም ፊተኛውና ኋለኛው ነኝ እኔም ለተጠማው ከሕይወት ምንጭ ይጠጣ ዘንድ ያለ ዋጋ እሰጠዋለሁ፡፡ ድል ለነሣውም ይህን ይወርሰዋል አምላኩ እሆነዋለሁ እርሱም ልጄ ይሆንልኛል፣ እያመኑ የፈሩት ግን ራሳቸውንም የሚያረክሱ የሚገድሉ የሚያመነዝሩ መተት ሥራይም የሚያደርጉ ጣዖትንም የሚያመልኩ ሐሰት የሆነውንም ሁሉ የሚናገሩ ፍዳቸው እሳትና ዲን ያለበት ገሃነም ይሆናል ይህም ሁለተኛ ሞት ነው፡፡ ዳን፲፪÷፱ ዕብ፲፫÷፰ ራእ፳፩÷፩፣፫-፰

፲፱ በኋላኞቹ ሰባት መቅሠፍቶች የተሞሉ ሰባት ጽዋዎችን ከያዙ ከእነዚያ መላእክት አንዱ መጣ፣ከእኔም ጋር ተነጋገረ የበጉን ሚስት ሙሽራይቱን አሳይህ ዘንድ ና አለኝ መንፈስም ወደ ረጅም ተራራ አወጣኝ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ የምትወርድ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌምን አሳየኝ የእግዚአብሔርም ክብር በእርሷ ላይ አለ ከዋክብቶቿም የከበረን ዕንቍን ይመስላሉ፡፡ እንደ ዕንቍም ነጭ ናት ግድግዳዋ ታላቅ ነው ግንቧም ረጅም ነው አሥራ ሁለት ደጃፎች አሏት በአሥራሁለቱም ደጃፎች አሥራ ሁለት መላእክት አሉ የአሥራ ሁለቱም የእስራኤል ወገኖች ስም ተጽፏል፡፡ ሦስት በስተምስራቅ ባሉ ደጃፎች ሦስት በስተምዕራብ ባሉ ደጃፎች፣የሀገሪቱም ግድግዳ መሠረቶቿ አሥራ ሁለት ናቸው የዐሥራ ሁለቱም የበጉ ሐዋርያት ስም በውስጣቸው ተጽፏል፡፡ ይህም ከእኔ ጋር የሚነጋገረው ያችን ከተማ ደጃፎቿንና ግድግዳዎቿን ይለካበት ዘንድ ዘንግ ይዟል፡፡ ከተማይቱም በርዝመቷም በወርዷም አራት ጎን ናት፡፡ ከተማይቱንም በዚያ ዘንግ ለካት መጠኗም ርዝመቷና ወርዷ አሥራ ሁለት ሺህ ምዕራፍ ሆነ ቁመቷም እኩል ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ግድግዳዎቿን ለካ በሰው ክንድ አንድ መቶ አርባ አራት በመልአክም ክንድ አንድ ሆነ ፡፡ ራእ፳፩÷፱-፲፯

፳ በከተማይቱም በግድግዳዎቿ ራስ ላይ የኢያስጵድ ዕንቍ አለ፣ከተማይቱም በጠራ ወርቅ እንደተሠራች ትመስላለች የከተማይቱም ግድግዳ መሠረት በከበረ ዕንቍ ሁሉ እንዳጌጠ ነጭ መቅረዝ ነው፡፡ ፊተኛዋም መሠረት የኢያስጲድ ሁለተኛይቱ የሰንፔር ሦስተኛይቱ የኬልቄዶን አራተኛይቱም የመረግድ አምስተኛይቱ የሰርዶንክስ ስድስተኛይቱ የሰርድዮን ሰባተኛይቱ የክርስቲሎቤ ስምንተኛይቱ የቢረሌ ዘጠነኛይቱ የወራውሬ ዓሥረኛይቱ የክርስጵስስ አሥራ አንደኛው የያክንት አሥራ ሁለተኛው የአሜትስጢስ ነው፡፡አሥራ ሁለቱ ደጃፎቿም በአሥራ ሁለት ዕንቍ ያጌጡ ናቸው እያንዳንዱም ደጅ በአንዲት ዕንቍ የተሠራ ነበር፡የከተ

ንጹሕ ዘያጸድል እንተ ውስጡ ማህው። ወኢር ኢኩ ጽርሐ እስመ እግዚአብሔር ዘኩሎ ይመልክ ውስተ ጽርሐ መቅደሱ ወበግዑ።ራእ፳፩፥፲፰-፳፪

፳፩ ለቡ ሊተ ኦ አብድ ነገረ ኅቡዓቲሁ ለአቡቀለምሲስ ኀበ ገጸ መጽሐፍ ዘላዕሉ ይቤ ወእምዝ ርኢኩ ሰማየ ሐዲሰ ወምድረ ሐዳሰ እስመ ሰሰለ ሰማይ ቀዳማዊ ወምድርኒ ቀዳሚት ወባሕርኒ ተሰዕረት እንከ።ወሀገርኒ ቅድስት ሐዳስ ኢየሩሳሌም ርኢክዋ ወረደት እምሰማይ እምኀበ እግዚአብሔር።ናሁኬ ነገረከ ዘከመ ሰሰለ ሰማይ ቀዳማዊ ወምድርኒ ቀዳማዊት ወዘከመ አስተርአየ ሰማይ ሐዲስ ወምድርኒ ሐዲስ። ወዘከመ ወረደት ኢየሩሳሌም እምሰማይ ዲበ ምድር እንተ ይእቲ ጽርሐ መቅደሱ ለእግዚአብሔር ወማኅደረ ቅድሳቲሁ ለስቡሐ እስራኤል።ወእምዝ ነገረ ሥነ ሕንጼሃ ወአምጣነ ኑኃ ወግድማ።ወአእባነ ባሕርይ ዘውስተ አናቅጺሃ ወእምዝ ይቤ ወኢርኢኩ ጽርሐ እስመ እግዚአብሔር ዘኩሎ ይመልክ ውስተ ጽርሐ መቅደሱ ወበግዑ።ሀገራሰ ኢትፈቅድ ፀሐየ ወወርኀ ከመ ያብርሁ ላቲ እስመ እግዚአብሔር ያበርህ ላቲ ወማኅቶቶተ በግዑ።ርኢኬ ርደተ ኢየሩሳሌም እምላዕሉ ኀበ ታሕቱ ምስለ አብ ወወልዱ፡ እስመ አቅደመ ረአዩ ኅቡዓቲሁ ነገረ ሥላሴሆሙ ለሰማያት ወምድር።ወእምዝ አትለወ ምጽአተ ኢየሩሳሌም ምስለ እግዚአብሔር ወበግዑ።መኑ ውእቱ እግዚአብሔር ዘእንበለ አምላክነ ወመኑ ውእቱ በግዑ ዘእንበለ አማኑኤል ዘኢይትፈለጥ እምህላዌ አቡሁ ።

፳፪ ተኅፈርኬ ኦ ረሲዕ ወደይ እዴከ ውስተ አፉከ።አአምር ከመ እመ ሀለዉ ምእመናኒከ ዘተሠውጠ ሕምዘ ትምህርትከ ውስተ ልቦሙ ይብሉኒ ሶበሰ ሀሎ ቢቱ ውእቱኒ እምተናገረ እምዝ ዘየዐቢ።ወአነሂ እብሎሙ እመሰኬ ቦቱ እምቃለ መጻሕፍት ዘይነግር በእንተ ኢመጺአ አብ ለምንትኬ አዕቀፀኒ በነገረ ጐሕሉት ወኢጸንዐ ለዕድሜ መዋዕል በዘአደመነ ንጉሥ።ኅደጋ ለገጸ መጽሐፍ ወነዐወኒ በነገረ ጐሕሉት።ወእመኒ ትብሉ ውእቱሰ ምውት ወአንተሰ ሕያው መኑኬ ይትዋሥአከ ወአነሂ እብለክሙ ዝኒ ፍትሐ ኩነኔሁ ለእግዚአብሔር ውእቱ።ሎቱሰ አፍጠነ እግዚአብሔር አሕጉሎቶ ከመ ኢይድብያ ለቤተክርስቲያን በከመ አስተፋጠነ ሞተ ንስጥሮስ።ሊተሰ ፀንሐኒ እግዚአብሔር እስከ እነግር ዘለፋ ሃይማኖቱ ወአስተጻንዖሙ ለመሀይምናን በቃለ መጻሕፍት ዘተወፈይኩ እምነቢያት ወሐዋርያት።

ማይቱ አደባባይ ጥሩ ብርጭቆ የሚመስል የጠራ ወርቅ ነበር።አዳራሽ አላየሁም ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔርና በጉ በመቅደሱ አዳራሽ አለና። ራእ፳፩፥፲፰-፳፪

፳፩ አንተ ሰነፍ ከላይ በተነገረው የመጽሐፍ ክፍል የአቡቀለምሲስን የምሥጢሮችን ነገር አስተውልልኝ። ከዚህ በኋላ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር አየሁ ፊተኛው ሰማይ ፊተኛይቱም ምድር አልፏልና ባሕርም ከእንግዲህ ተሽራለች፣ ቅድስቲቱ ከተማ አዲሲቷም ኢየሩሳሌም ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ አለ። እነሆ ፊተኛው ሰማይ ፊተኛይቱም ምድር እንዳለፈች አዲስ ሰማይና አዲስ ምድርም እንደታየ ኢየሩሳሌምም ከሰማይ ወደ ምድር እንደወረደች ነገረህ ይህችውም የእግዚአብሔር የመቅደሱ አዳራሽ የእስራኤልም ቅዱስ የቅድስናው ማደሪያ ናት። ከዚህም የሕንፃዋን ማማር የርዝመቷንና የወርዷን መጠን በደጃፎቿም ላይ ስላሉት የከበሩ ደንጊያዎች ተናገረ። ከዚህም አዳራሽ አላየሁም ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔርና በጉ በመቅደሱ አዳራሽ አለና፣ከተማይቱም ያበሩላት ዘንድ ፀሐይና ጨረቃን አትሻም እግዚአብሔር የበጉም መብራት ያበራላታልና አለ። የኢየሩሳሌምን ከአብና ከልጁ ጋር ከላይ ወደ ታች መውረድ ተመልከት ምሥጢራትን ያየ እርሱ ለሰማያትና ለምድር የሦስትነታቸውን ነገር አስቀደመ ከዚያም የኢየሩ ሳሌምን ከእግዚአብሔርና ከበጉ ጋር መምጣት አስከተለ። ከአምላካችን በቀር እግዚአብሔር ማን ነው ከአባቱስ ህልውና ከማይለወጥ ከአማኑኤል በቀር በጉ ማን ነው።

፳፪ ዝንጉ ሆይ እፊር እጅህንም በአፍህ ላይ አኑር የትምህርትህ መርዝ በልባቸው ውስጥ የተሠራጨ ተከታዮችህ ቢኖሩ ኖሮ ቢቱ ቢኖር ከዚህም የሚበልጥ በተናገረ ነበር እንደሚሉኝ ዐውቃለሁ፡ እኔም ከመጻሕፍት ቃል ስለአብ አለመምጣት የሚናገር ካለው በሽንገላ ቃል ስለምን አስናከለኝ ንጉሥ በቀጠረን ዕድሜ ጊዜ ለምን አልቆየም፡ የመጽሐፍን ገጽ ተዋት እኔንም በሽንገላ ቃል አጠመደኝ እላችዋለሁ። እርሱ ሞቷል አንተ ግን በሕይወት አለህ ማን ይመልስልህል ብትሉኝ እኔም ይህ የእግዚአብሔር ፍርዱ ነው እላችኋለሁ፡ ቤተ ክርስቲያንን ከትቢያ እንዳይጥላት የንስጥሮስን ሞት እንዳፋጠነ የእርሱን ጥፋት አፋጠነ። እኔ ግን የሃይማኖቱን ዘለፋ እስክናገር ምእመናንንም ከነቢያትና ከሐዋርያት በተቀበልሁት የመጻሕፍት ቃል እስካበረታቸው ድረስ እግዚአብሔር አቆየኝ።

፳፫ ወእመሂ ትብሉኒ አንተሂ ትመውት ከማሁ፡፡ወአነሂ እብለክሙ እስመ ኢሠርዐ ሊተ እግዚአብሔር ሕይወተ ከመ መላእክት ከመ ኢይጥዐሞ ለሞት አላ ጸንሐኒ እስከ እነግር ዘለፋሁ ለዘክሕደ ምጽአቶ ዝ ውእቱ ዓቅምየ፡፡ ወእምይእዜሰ ይግበር እግዚአብሔር ዘይዔድሞ በቅድመ አዕይንቲሁ፡፡ በከመ ይቤ ጳውሎስ እመኒ ሐየውነ ለእግዚአብሔር ነሐዩ ወእመኒ ንመውት ለእግዚአብሔር ንመውት ፡፡እንከሰኬ እብል ጸዋዕክዎ ለእግዚአብሔር ወተሰጥወኒ ኀሠሥክዎ ወረከብክዎ ጉድጉ ድኩ ወተርኅወ ሊተ፡፡ ወእመሂ ፈለስኩ እምዝ ዓለም አኮ ዘይከውን ንግደተ ቢቱ ውእቱሰ ይቀውም ኀበ ዘክሕደ ምጽአቶ ወአንሰ እቀውም ኀበ ዘአ መንኩ ቦቱ፡፡ መዝ ፴፫፥፫ ሮሜ፲፬፥፰

፳፬ እልቦ እንከ ዘተንሥአ እምቅድ መዝ ዕልው ዘከመ ቢቱ፡፡ወሰብልያኖስኒ ተሰ ምየ ዕልው በእንተ ዘቶስሐ ጽምረተ ሥላሴ፡፡ አቡርዮስኒ በእንተ ዘዘረወ፡፡አርጌንስኒ በእንተ ዘመሀረ ሑፃጌ ወልድ እም አብ፡፡ወፎጢኖስኒ በእንተ ዘአስተደኀረ ህላዌ መለኮተ ወልድ እመለኮተ አብ፡፡አርዮስኒ ወንስጥሮስ ወመ ንኪዮን ወአፍቲክስ ልዮን ወማኅበረ ኬልቄዶን ተሰምዩ ዕልዋነ በእንተ ዘነበቡ ጽርፈተ ላዕለ ወልደ እግዚአብሔር፡፡ወለቢቱሰ ሰመይ ናሁ ዕልወ በእንተ ዘክሕደ ምጽአተ አብ፡፡ በከመ አብ ይሰመይ አበ ለኩሉ ለዘይገብር ሠናየ ወከማሁ ለቢቱኒ ንሰምዮ አበ ለረሲዓን ወርእሰ ለዕልዋን፡፡ወንብሎ እንከ አበ ስሕተት ወአበ ሐሰት አበ ጉሕሉት ወአበ ትምይንት አበ ዓመፃ ወአበ ጽልሑት አበ በቀል ወአበ ቂም ወቅን ዓት፡፡ወልዱ ለሰይጣን ወእኁሆሙ ለአጋንንት ወአቡሆሙ ለከሐድያን ወመምህሮሙ ለመናፍቃን፡፡አስካሉኒ አስካለ ሐሞት ወሕምዘ አፍዖት ወይኑ፡ወቀምኁኒ መሪር ወሞጻሕቱኒ ደመ ዕጉስታር፡እስመ ከመ ዓጸደ ወይነ ሰዶም ዓጸደ ወይኑ ወሐረጉኒ እምነ ገሞራ፡፡

፳፭ ንንግር እንከ በእንተ ፍና ምጽ አቱ ለወልደ እግዚአብሔር እስመ ሠላስ እማ ንቱ፡፡ቀዳሚ ኀበ ንጽሕት ድንግል ለተሠግ ዎ፡፡ወዳግም ከመ ይትበቀሎ ለሐሳዌ መሲሕ ወለእለ ተኀትሙ በማኅተመ ዚአሁ ወእምዝ ይገብር ምሳሐ ለቅዱሳነ ልዑል፡፡በከመ ይቤ ዮሐንስ አቡቀለምሲስ ወይቀውም ሎሙ ውእቱ በግዕ ውስተ ደብረ ጽዮን፡፡ወበእንተ ሠላስ ፍና ምጽአቱ ዜነወ ጳውሎስ ፈልፈለ

፳፫ አንተም እንደርሱ ትሞታለህ ብትሉኝ እግዚአብሔር እንደ መላእክት ሞትን እንዳልቀምሰው ሕይወትን አልፈጠረልኝም መምጣቱን የካደ የእርሱን ዘለፋ እስክነግር አቆ የኝ እንጂ አቅሜ ይህ ነው ከእንግዲህስ እግዚአብሔር ጳውሎስ በሕይወት ብንኖር ለእግዚአብሔር ነን ብንሞትም ለእግዚአብሔር እንሞታለን እንዳለ እግዚአብሔር በዓይኖቹ ፊት የወደደውን ያድርግ ከእንግዲህ እላለሁ እግዚ አብሔርን ጠራሁት መለሰልኝም ፈለግሁት አገኘ ሁትም አንኳኳሁ ተከፈተልኝም ከዚህም ዓለም ባልፍ አካሄዴ እንደ ቢቱ አካሄድ የሚሆን አይደለም እርሱ መምጣቱን በካደው በእርሱ ፊት ይቆማል እኔ ግን ባመንሁበት በእርሱ ፊት እቆማለሁ፡፡ መዝ ፴፫፥፫ ሮሜ፲፬፥፰

፳፬ እንግዲህ ከዚህ በፊት የተነሣ እንደ ቢቱ ያለ ከሀዲ የለም እኮን ሰብልያኖስም በሥላሴ አንድነት ላይ ስለጨመረ ከሀዲ ተባለ አቡርዮስም ስለ በተነ፣ አርጌንስ የወልድን ከአብ ማነስ ስላስተማረ ፎጢኖስም የወልድን መለኮት ህልውና ከአብ መለኮት ወደ ኋላ ስላደረገ አርዮስና ንስጥሮስ መንኪዮንና አፍ ቲክስ ልዮንና የኬልቄዶን ማኅበረተኞች በእግ ዚአብሔር ልጅ ላይ ስድብን ስለተናገሩ ከሀ ዲዎች ተባሉ፡፡ ቢቱንም የአብን መምጣት ስለካደ ከሀዲ ብለን ጠራነው፡ አብ በጎ ለሚያ ደርግ ሁሉ አባት እንደሚባል እንዲሁ ቢቱንም የዝንጉዎች አባት የከሀዲዎችም ራስ እንለዋለን ከእንግዲህም የስህተት አባት የሐሰት አባት የሽንገላ አባት የመተንኳኮል አባት የዓመፃ አባት የተንኮል አባት የበቀል አባት የቂምና የቅናት አባት የሰይጣን ልጅ የአጋንንት ወንድ ማቸው የከሀዲዎች አባታቸው የመናፍቃን መምህራቸው ብለን እንጠራዋለን፡፡ ፍሬው የሐሞት ፍሬ ወይኑ የእፉኝት መርዝ ነው፡፡ ፍሬው የሚጉመዘዝ ወይኑም የእሬት ደም ነው የወይን ቦታው እንደ ሰዶም የወይን ቦታ ሐረጉም ከገሞራ የተገኘ ነውና፡፡

፳፭ እንግዲህስ ስለ እግዚአብሔር ልጅ አመጣጡ እንናገር ሦስት ናቸው መጀ መሪያ ሰው ለመሆን ወደ ንጽህት ድንግል መጣ ሁለተኛም ሐሳዌ መሲሕንና በማኅተሙ የታተ ሙትን ሊበቀል ይመጣል ከዚህም በኋላ ለልዑል ቅዱሳን ምሳ ያደርጋል ዮሐንስ አቡቀለምሲስ በጉም በጽዮን ተራራ ላይ ይቆምላቸዋል እን ዳለ፡፡ ስለ ሦስተኛው አመጣጦቹ የጥበብ ምንጭ ጳውሎስ ተናግሯል፡፡ ስለ መጀመሪያይቱ

ጥበብ፡፡ በእንተ ቀዳሚት ምጽአቱ ይቤ ወመጽአ እምዘርአ ዳዊት በሥጋ ሰብእ፡፡ወካዕበመ ይቤ እንዘ ይፌክር በቃለ ሰላም ለመኑ እመላእክት ይቤሎሙ እምአመ ኮነ ወልድየ አንተ ወአነ ዮም ወለድኩከ፡፡ወካዕበ ይቤ አነ እከውኖ አባሁ ወውእቱኒ ይከውነኒ ወልድየ፡፡ወበመትልወ ዝንቱ ቃል ይቤ ጳውሎስ ወአመ ካዕበ ፈነዎ ለበኩሩ ውስተ ዓለም ይቤ ወይሰግዱ ሎቱ ኩሎሙ መላእክተ እግዚአብሔር፡፡ዘንተስ ይቤ በእንተ መንግሥተ ደብረ ጽዮን፡፡ ለእለሰ ይብሉ አልቦ ምሳሐ ደብረጽዮን መሐልኩ እዴሁ ለኢየሱስ ክርስቶስ ከመ አልቦሙ መክፈልተ እምሳሕ ዘ፲፻ ዓመት በከመ ይቤ በመዝሙር ዘአበያ ለበረከት ትርሕቅ እምኔሁ፡፡መዝ፹፱÷፳፮፥፻፲÷፲፯ ሮሜ፩÷፩ ዕብ፩÷፭ ፮

፳፪ ጳውሎስኒ ነገረ በእንተ መንግሥተ ደብረ ጽዮን ወይቤ ወአመ ይትነሥኡ ምውታን እለ በክርስቶስ ይቀድሙ ፡፡ወእምዝ ንሕነ እለ ሕያዋን ተረፍነ ይመሥጡነ በደመና ከመ ንትቀበሎ ለልዑል ወነሀሉ ዘልፈ ኀበ እግዚእነ፡፡ በእንተ ምንትኬ ይቤ ጳውሎስ እለ በክርስቶስ ይቀድሙ፡ነገረኬ በሊሐ ኅሊና ወበሊሐ ልሳን ከመ ይቀድም ትንሣኤ ለእለ ይደልዎሙ ምሳሐ ኢየሱስ ክርስቶስ፡፡ ወዘይቤሰ ወእምዝ ንሕነ እለ ሕያዋን ተረፍነ ይመሥጡነ በደመና ከመ ንትቀበሎ ለልዑል፡፡ ዘንተኒ ነገረ በእንተ ዘሀለዎሙ ይትመሠጡ በደመና ከመ ይኩኑ ሱቱፋነ ለምሳሐ ደብረ ጽዮን፡፡ አኮሰ ዘጥዕመ ሞተ ጳውሎስ አላ ሕይወተ ዚአሁ ይሬሲ ሕይወቶሙ ለእለ ሀለዎሙ ይትመ ሠጡ ሕያዋኒሆሙ በከመ ይቤ ለሊሁ ንሕነሰ ንመውት ከመ አንትሙ ትሕየዉ፡፡ ወእግዚእነሂ ይቤ በወንጌል ፪ ይሰክቡ ውስተ ፩ አራት ፩ ይነሥኡ ወካልዖ የኅድጉ፡፡እለሰ ውስተ ፩ አራት ይሰክቡ ፪ እምጻማ ዓለም፡፡ ለ፩ ይመሥጥዎ በእንተ ዘይደልዎ ምሳሐ ደብረ ጽዮን ወለ፩ ዕደው አብዕልት እሙንቱ እለ ዕሩፋን የኅድግዎ በእንተ ዘኢይደልዎ፡፡ እመሰ ኮነ ፩ አራቶሙ ኢኮነ ምግባሮሙ፡፡ ወካዕበመ ይቤ ክልዔቲ የኀርጻ ውስተ አሐቲ ማኅረጽ አሐተ ይነሥኡ ወካልዕታ የኅድጉ፡፡ ይነሥእዋ ለዘይደልዋ ምሳሐ ደብረ ጽዮን ወየኅድግዋ ለዘኢይደልዋ፡፡እመሰ ኮነ ፩ ጻማሆን ኢኮነዕሩየ ሥነ ምግባሮን፡፡ ወዓ ዲመ ይቤ ፪ ይሄልው ውስተ አሐቲ ገራ ህት ፩ ይነሥኡ ወካልአ የኅድጉ መስተ ገብራን እሙንቱ ለ፩

አመጣጡ በሰው ሥጋ ከዳዊት ዘር መጣ አለ፡፡ ሁለተኛም በሰላም ቃል ሲተረጉም ከሆነ ጀምሮ ከመላእክት ወገን ማንን አንተ ልጄ ነህ እኔም ዛሬ ወለድሁህ አለው ሁለተኛም እኔ አባቱ እሆነዋለሁ እርሱም ልጄ ይሆንልኛል አለ፡፡ ከዚህም ቃል በማያያዝ ጳውሎስ ዳግመኛም በኲሩን ወደ ዓለም በላከው ጊዜ የእግዚአብሔር መላእክት ሁላቸው ይሰግዱለታል አለ ይህንን በጽዮን ተራራ ስለሚገለጥ መንግሥቱ ተናገረ፡፡ በጽዮን ተራራ ምሳ የለም ለሚሉት ዳዊት በመዝሙር በረከትን እንቢኝ ያለ ከእርሱ ትራቅ እንዳለ ከሺህ ዓመት ምሳ እድል ፈንታ እንደሌላቸው በኢየሱስ ክርስቶስ እጅ ማልሁ፡፡ መዝ፹፱÷፳፮፥፻፲÷፲፯ ሮሜ፩÷፩ ዕብ፩÷፭ ፮

፳፫ ጳውሎስም ስለ ድብረ ጽዮን መንግሥት በክርስቶስ አስቀድመው የሞቱ በሚነሡ ጊዜ በሕይወት የቆየን እኛን ልዑልን እንቀበለው ዘንድ በደመና ይነጥቁናል ለዘላለምም በጌታችን ዘንድ እንኖራለን ብሎ ተናገረ፡፡ ጳውሉስ ስለምን በክርስቶስ የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ አለ፤ ኅሊናው የተሳለ አንደበቱም ስል የሆነ እርሱ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳ ለሚገባቸው ትንሣኤ እንደሚቀድም ተናገረ፡ከዚህም በኋላ በሕይወት የቀረን እኛን ልዑልን እንቀበለው ዘንድ በደመና ይነጥቁናል አለ፡፡ ይህንንም በጽዮን ተራራ ምሳ የሚሳተፉ ሲሆኑ በደመና ይነጠቁ ዘንድ ስላላቸው ሰዎች ተናገረ፡፡ ጳውሉስ ሞትን የቀመሰ አይደለም የርሱን ሕይወት በሕይወታቸው ይነጠቁ ዘንድ ላላቸው ሰዎች ሕይወት አደረገ እንጂ፡እርሱ ራሱ እኛ ግን እናንተ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ እንሞታለን እንዳለ፡፡ ጌታችንም በወንጌል ሁለት ሰዎች በአንድ አልጋ ይተኛሉ አንዱን ይወስዱታል ሁለተኛውንም ይተዋሉ አለ፡፡ በአንድ አልጋ ላይ የሚተኙት ከዓለም ድካም ያረፉ ሁለት ባለጠጎች ናቸው አንዱን የጽዮን ተራራ ምሳ ስለሚገባው ይነጥቁታል ሁለተኛውንም ስለማይገባው ይተዉታል አልጋቸው አንድ ቢሆንም ሥራቸው አንድ አልሆነም፡ ሁለተኛም ሁለት ሴቶች በአንድ ወፍጮ ይፈጫሉ አንዲቱን ይወስዱሉ ሁለተኛይቱንም ይተዋሉ አለ፡፡ የደብረ ጽዮን ምሳ የተገባትን ይወስዷታል ያልተገባትን ግን ይተዉአታል፡፡ ድካማቸው አንድ ቢሆንም በጎ ሥራቸው የተካከለ አልሆነምና፡፡ ዳግመኛም ሁለት ሰዎች በአንድ እርሻ ይውላሉ አንዱን ይወስዳሉ ሁለተኛውን ይተዋሉ አለ፡፡ ገበሬዎች ናቸው አንዱን የደብረጽዮን ምሳ ስለሚገባው ይነጥቁታል አንዱን ግን ስለማይገባው ይተዉታል፡፡ ለእርሻ ሥራ ማገልገላቸው እኩል

ይመስጥዎ በእንተ ዘይደልዎ ምሳሐ ደብረ ጽዮን ወለ፩ የኀድግዎ በእንተ ዘኢይደልዎ፡፡ እመሰ ኮነ ዕሩየ ተቀንዮቶሙ ለተግባረ ገራውህ ኢኮነ ዕሩየ ተቀንዮቶሙ ለተግባረ ምግባረ ሠናይ፡፡ ማቴ፳፬÷፴ ፩ቆሮ፲፭÷፶፪ ፩ተሰ፬÷፲፮

፳፯ አእምሩኬ ወለብዉ ከመ ይትመሰጡ ሕያዋኒሆሙ እለ አስመርዎ ለልዑል ከመ ይኩኑ ሱቱፋነ ለምሳሐ ደብረ ጽዮን ፡፡ወእምድረዝ ይቤ ጳውሎስ ወእለሂ ተረፍነ ይመስጡነ በደመና ከመ ንትቀበሎ ለልዑል ወነሀሉ ዘልፈ ኀበ እግዚእነ:ወእምዝ አትለወ ወይቤ ወይእዜኒ መሀሩ ቢጸክሙ ዘንተ ነገረ: በእንተሰ ዕለቱ ወዕድሜሁ ወጊዜሁ አኀዊነ ኢይትፈቀድ ንጽሐፍ ለክሙ ለሊክሙ ተአምሩ ጥዩቀ ከመ ዕለተ እግዚእነ ከመ ሰራቂ ሌሊተ ይውከውን ምጽአቱ አመይብሉ ዳኅን ወሰላም ወግብተ ይመጽኦሙ ተሠርዎ ከመ እንተ ፅንስት እንተ ይመጽኣ ማሕምም፡፡ ዘንተሰ ይቤ በእንተ ምጽአት ሣልሲት እንተ ይእቲ ፍዳ ኃጥአን ወዕሤተ ጻድቃን፡፡ ማቴ፳፭÷፴፩

፳፰ ዮሐንስ አቡቀለምሲስኒ ይቤ ወእምዝ ተርኅወ ሰማይ ወወጽአ ፈረስ ጸዓዳ ወዘይጼዐኖ ስሙ መሀይምን ወጻድቅ ዘበጽድቅ ይኴንን ወይፀብእ፡፡ወአዕይንቲሁኒ ከመነደ እሳት ወዲበ ርእሱ አክሊል ወጽሑፍ ውስተ ቀጸላሁ አስማት ወአልቦ ዘየአምሮ ዘእንበለ ው እቱ ባሕቲቱ፡፡ወይለብስ ልብሰ ዘንዙኅ በደም ወሰመዩ ስሞ ቃለእግዚአብሔር ወሐራ ሰማይ ይትል ውዎ በአፍ ራስ ጸዓዳ ወይለብሰ ሜላተ ብርሃን ንጹሐ፡፡ወይወፅእ እምነ አፉሁ ሰይፍ በሊሕ ዘቦቱ ይቀሥፎሙ ለአሕዛብ ወውእቱ ይሬዕዮሙ በበትረ ሐጺን፡፡ወውእቱ ይከይዳ ለምክያደ ወይን ሕምዘ መዓቱ ለእግዚአብ ሔር ዘኩሎ ይመልክ፡፡ወጽሑፍ ውስተ ገቦሁ ስም ዘይብል ንጉሠ ነገሥት ወእግዚአ አጋ እዝት፡፡

፳፱ ወእምዝ ቆመ ፩ መልአክ ውስተ ፀሐይ ወፀርሐ በቃል ዓቢይ ወይቤ ለኩሉ አዕዋፍ ዘይሰርር ማእከለ ሰማይ ንዑ ተጋብኡ ውስተ በዓሉ ለእግዚአብሔር ዐቢይ ከመ ትብልዑ ሥጋ ነገሥት ወሥጋ ጽኑዓን ወሥጋ አፍራስ ወዘእለይጼዓንዎሙ ወሥጋ ኩሉ አግዓዚ ወገብር ወዘንኡስ ወዘዐቢይ፡፡ወእምዝ መጽአ ዝክቱ ወነገሥተ ምድር ወሠራዊቶሙ ተጋብኡ ምስሌሁ ከመ ይፅብእዎ ለዝክቱ አርዌ ዘይጼዓን ላዕለ ፈረስ ጸዓዳ ወለሠራዊቱ፡፡ ወእ

ቢሆንም በጎ ሥራ ለመሥራት መገዛታቸው የተካከለ አልሆነምና፡፡ ማቴ፳፬÷፴ ፩ቆሮ፲፭÷፶፪ ፩ተሰ፬÷፲፮

፳፯ ልዑልን ያገለገሉት በደብረ ጽዮን ምሳ የሚሳተፉ ሲሆኑ በሕይወታቸው ሳሉ እንደሚነጠቁ ዕወቁ አስተውሉም፡፡ ከእነ ዚህም በኋላ ጳውሎስ ሕያዋን ሆነን የቀረነውንም ልዑልን ልንቀበለው ዘወትርም በጌታችን ዘንድ ልንኖር በደመና ይነጥቁናል አለ፡፡ ከዚህም አያይዞ አሁንም ስለዚህ ነገር ለባልን ጀሮቻችሁ አስተምሩ አለ፡፡ስለቀኑና ስለ ዘመኑ ስለጊዜውም ወንድሞቻችን እንጽፍላችሁ ዘንድ አይገባም የጌታችን ቀን ደኅና ነው ሰላም ነው ሲሉ መምጣቱ እንደ ሌባ በሌሊት እንደሆነ ታውቃላችሁ የፀነሰች ሴት ምጥ ድንገት እንደሚመጣባት ጥፋት በድንገት ይመጣባቸዋል፡፡ ይህንን ስለሦስተኛይቱ መምጣት ተናገረ ይኸውም የኃጥአን ፍዳ የጻድቃንም በጎ ዋጋ ነው፡፡
ማቴ፳፭÷፴፩

፳፰ ዮሐንስ አቡቀለምሲስም አለ ከዚህም በኋላ ሰማይ ተከፈተ ነጭ ፈረስ ወጣ የተጫነበትም ስም ምእመንና ጻድቅ በጽድቅም የሚፈርድ የሚዋጋም ነው ዓይኖቹም እንደ እሳት ነድ ነው፡፡ በራሱም ላይ አክሊል አለ በመጠምጠሚያው ላይ ስም ተጽፏል ከእርሱም በቀር የሚያውቀው የለም በደም የተነከረ ልብስ ለብሷል ስሙንም የእግዚአብሔር ቃል ብሎ ጠራው የሰማይ ሠራዊት በነጭ ፈረስ ይከተሉታል ንጹህ የብርሃን ግምጃ ለብሷል ከአፉም አሕዛብን የሚቀሥፍበት የተሳለ ሰይፍ ይወጣል እርሱም በብረት ዘንግ ይጠብቃቸዋል ሁሉን በሚገዛ በእግዚአብሔር የቁጣው መርገዝ የወይን መጥመቂያ ይረገጡታል በጉኑም የንጉሦች ንጉሥ የጌቶችም ጌታ የሚል ስም ተጽፏል፡፡

፳፱ ከዚህም በኋላ አንድ መልአክ በፀሐይ ላይ ቆመ በታላቅ ድምፅም ጮሆ ከሰማይ በታች የምትበርሩ ወፎች ሁሉ ኑ የነገሥታትን ሥጋ የመላእክትንም ሥጋ የብርቱዎችን ሥጋ የፈረሶችን የሚጫኑባቸውንም ሥጋ የገዢውንና የባሪያውን የታናሹንና የታላቁንም ሥጋ ትበሉ ዘንድ ወደታላቁ ወደ እግዚአብሐር በዓል ኑ ተሰብሰቡ አለ፡፡ ከዚህም በኋላ እርሱ መጣ፡፡ የምድር ነገሥታትና ሠራዊቶቻቸው በነጭ ፈረስ ላይ የተጫነውን ያንን አውሬና ሠራዊቱን ይወጉት ዘንድ ተሰበሰቡ፡፡ ከዚህም በኋላ ያንን አውሬ እነርሱን ያስታቸው

ምዝ እኅዝዎ ለዝክቱ አርዌ ወለሐሳዌ ነቢይ ዘገብረ ተአምረ በቅድሜሁ በዘያስሕቶሙ ለእሉ ወተጽሕፈ ስመ ማኅተሙ ለውእቱ ወሰገዱ ሎቱ ወለምስሉ፡፡ወወደይዎሙ ሕያዋኒሆሙ ውስተ ዓዘቅተ እሳት ዘይነድድ በተይ፡፡ ወለእለሰ ተርፉ ቀተልዎሙ በሰይፉ ለዝክቱ ዘይጼዓን ላዕለ ፈረስ ጸዓዳ እንተ ትወጽእ እምአፉሁ ሰይፍ በሊሕ ውእቱ፡፡ወጸግቡ ኩሉ አዕዋፍ እምነ ሥጋሆሙ፡፡ራእ፲፱፥፲፩-፳፩

፴ ወእምዝ ወረደ ካልዕ መልአክ እምሰማይ ወይጸውር መራኁተ ፀሐይ ወዐበይት መዋቅሕት ውስተ እዴሁ፡፡ወአኀዞ ለዝክቱ አርዌ ዘውእቱ ቀዳማዊ ወውእቱ ጋኔን ሰይጣን፡፡ወአሰሮ ፲፻ ዓመተ፡፡ወእምድኅረ ዝንቱ ሀለዎ ይፍትሖ ሕዳጠ መዋዕለ፡፡ወእምዝ ርኢኩ መናብርተ ወነበረ ላዕሌሆሙ ወልደ እጓለ እመሕያው፡፡ ወአግብአ ሎሙ ፍትሐ በእንተ ነፍሶሙ ለእለ ተቀትሉ በእንተ ሕጉ ለኢየሱስ ክርስቶስ በእንተ ቃለ እግዚአብሔር፡፡ ለእለሰ ኢሰገዱ ለውእቱ አርዌ ወኢለምስሉ ወኢጸሐፉ ትእምርቶ ውስተ ፍጽሞሙ ወኢውስተ እዴሆሙ እሙንቱ የሐይዉ ወይነግሡ ምስለ ክርስቶስ ፲፻ ዓመተ፡ናሁኬ በዝ አያቀ ዳግማየ ምጽአተ ወልድ ውስተ ደብረ ጸዮን ደብረ ምርፋቆሙ ለቅዱሳን፡፡ራእ፳፥፩-፬

፴፩ ወእምዝ አትለወ ወይቤ ወእምዝ ሰሰለ ሰማይ ቀዳማዊ ወምድርኒ ቀዳማዊት፡፡ ናሁኬ አርአየ መንግሥተ እንተ ትመጽእ እንተ ትትመከዐብ እምጽአት ኀበ ደብረ ጽዮን ወእንተ ትሤለስ እምጽአት ኀበ ሥጋዌ፡፡ምጽአትሰ ኀበ ሥጋዌ ለመድኃኒተ ዓለም ኮነት፡፡ ወምጽአትሰ ሣልሲት ለፍዳ ኃጥአን ወለዕሤተ ጻድቃን፡ወበእንተዝ ይቤ ሙሴ ይነግሥ እግዚአብሔር ለዓለም ወለዓለመ ዓለም ወዓዲ፡፡ይነግሥ እግዚአብሔር ለዓለም ይቤ በእንተ ዛ ዓለም ዘሀሎነ ባቲ፡፡ወለዓለመ ዕለም ይቤ በእንተ መንግሥተ ደብረ ጽዮን ወዓዲ ይቤ በእንተ ዓለም እንተ ትመጽእ በግርማ መንግሥቱ ለአብ፡፡እንተ ኢትትኌለቍ በሐሳብ ወአልባቲ ዕድሜ ዓመታት ወኢኩፋሌ መዋዕል፡፡ ወእግዚእነሂ ይቤ በወንጌል አልቦ ዘየኀድግ አብያተ ወአኃወ ወአኃተ አበ ወእመ ወብእሲተ ወውሉደ ወገራውሀ በእንቲአየ ወበእንተ ወንጌልየ ዘኢይትዔሠይ ፻ ምክዕቢተ በዝንቱ ዓለም ወአብያተ ወአኃወ ወአኃተ ወአበ እመ

ዘንድ በፊቱ ምልክትን የደረገውን አሰተኛውን ነቢይ ያዙት፡የእርሱም የስሙ ማኅተም ተጻፈ ለርሱና ለምስሉ ሰገዱ፡፡ በዲን ወደሚነደው የእሳት ጉድጓድ ከነሕይወታቸው ጨመሩአቸው የቀሩትንም በነጭ ፈረስ ላይ በሚጫነው ከአፉም የተሳለ ሰይፍ በሚወጣው በርሱ ሰይፍ ገደሉአቸው ወፎችም ሁሉ ከሥጋቸው ጠገቡ፡፡

፴ ከዚህም በኋላ ሌላ መልአክ ከሰማይ ወረደ፡ የፀሐይ መክፈቻዎችን ይዟል ታላቅም ሰንሰለት በእጆቹ አለ፡ ፊተኛውንም አውሬ ያዘው፡ እርሱም ጋኔን ሰይጣን ነው ሺህ ዓመትም አሠረው ከዚህ በኋላ ጥቂት ጊዜ ይፈታው ዘንድ አለው፡፡ ከዚህ በኋላ ዙፋኖች አየሁ በላያቸውም የሰው ልጅ ተቀምጦ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕግ ስለ እግዚአብሔርም ቃል ለተገደሉት ሰዎች ነፍሳት ተፈረደላቸው ለአውሬውና ለምስሉ ያልሰገዱትና ምልክቱንም በግምባራቸው በእጃቸውም ያልጻፉት እነርሱ በሕይወት ይኖራሉ ከክርስቶስም ጋር ሺህ ዓመት ይነግሣሉ እነሆ የወልድን የቅዱሳን መቀመጫ ተራራ ወደሆነች ወደ ደብረ ጽዮን መምጣት በዚህ አስታወቀ፡፡ ራእ፳፥፩-፬

፴፩ ከዚህም አስከትሎ ከዚህ በኋላ ፊተኛው ሰማይ ተወገደ ፊተኛይቱም ምድር አለፈች አለ፡ እነሆ የምትመጣዋን ወደ ደብረ ጽዮን ከመምጣት እጽፍ ድርብ የሆነችውን ሰው ለመሆን የመምጣት ሦስተኛ የሆነችይቱን መንግሥት ገለጠ፡፡ ሰው ለመሆን መምጣት ለዓለም ድኅነት ሆነች፡፡ ሁለተኛዋ መምጣት ለቅዱሳን ተድላ ናት ሦስተኛዋ መምጣት ግን ለኃጥአን ፍዳ ለጻድቃን በጎ ዋጋ ናት፡፡ ስለዚህም ነገር ሙሴ እግዚአብሔር ለዘላለም ይነግሣል ዳግመኛም እግዚአብሔር ለዘላለም ይነግሣል አለ፡፡ ስላለንባት ስለዚህች ዓለም ተናገረ፡፡ ለዘላለም አለ ስለ ደብረ ጽዮን መንግሥት ዳግመኛም በአብ የመንግሥት ግርማ በቁጥር የማትቆጠር ስለ ዓለም ነው፡፡ የዓመታት ዕድሜ የዘመን መከፈልም የላትም፡ ጌታችን በወንጌል ስለ እኔ ስለ ወንጌልም ቤቶችንና ወንድሞችን እኅቶችን አባትና እናትን ሚስትንና ልጆችን እርሻዎችን የሚተው በዚህ ዓለም መቶ እጥፍ የማይቀበል የለም ቤቶችንና ወንድሞችን እኅቶችን አባትና እናትን ልጆችንና እርሻዎችን

ወውሉደ ወገራውሀ በስደት፡፡ወበዓለምሰ ዘይመጽእ ሕይወተ ዘለዓለም፡፡ ዘጸ፲፭÷፲፰ ማቴ፲፱÷፴

፴፪ አልቦ ዘኢይትዔሠይ ፻ ምክዕቢተ በዝ ዓለም ዘይቤ በእንተ መንግሥተ ደብረ ጽዮን፡፡ወበዓለምሰ ዘይመጽእ ሕይወተ ዘለዓለም ዘይቤ በእንተ መንግሥተ ሰማያት ዘምጽአተ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ ዘሎቱ ስብሐት ለዓለመ ዓለም አሜን: አሜን: ወአሜን፡፡

፴፫ ተፈጸመ ዘለፋሁ ለቢቱ ሙሱነ ሃይማኖት በትምህርቱ፡ወልደ ዲያብሎስ በትዕቢቱ፡ዘይትከሐዶ ለአብ በእንተ ምጽአቱ፡ ይቤ ጊዮርጊስ ጽዩአ ምግባር በኃጢአቱ፡ ርቱዐ ሃይማኖት በእምነቱ፡መስተባእስ ምስለ ዕልዋን በቅንዐቱ፡ ወይትግህ ለዘለፋሆሙ በአምጣነ ክሂሎቱ፡ ወይትወለተው በስመ ሥላሴ በአምልኮቱ፡ አሚን ወትውክልት አሕፃሁ ወቀሥቱ፡ ስብሐት ለእግዚአብሔር እስመ ተለዓለ ስሙ ለባሕቲቱ፡ለዓለመ ዓለም አሜን: አሜን: ወአሜን ለይኩን: ለይኩን: ለይኩን፡፡

........ /// ..........

በስደት የሚተው በሚመጣው ዓለም የዘላለም ሕይወት ይወርሳል አለ፡፡ዘጸ፲፭÷ ፲፰ ማቴ፲፱÷፴

፴፪ በዚህ ዓለም መቶ እጥፍ የማይቀበል የለም ያለው ስለ ደብረ ጽዮን መንግሥት ነው በሚመጣው ዓለም ግን የዘላለም ሕይወት ያለው ስለ አብና ወልድ ስለ መንፈስቅዱስም መምጣት ስለ መንግሥተ ሰማያት ነው፡፡ ለርሱ ምስጋና ይገባል ለዘላለሙ አሜን

፴፫ በትምህርቱ ሃይማኖቱ የጠፋ በትዕቢቱ የዲያብሎስ ልጅ የሆነ አብን ስለመምጣቱ የካደው የቢቱ ተግሣጽ ተፈጸመ፣ በኃጢአቱ ሥራው የተበላሸ በእምነቱ ግን ሃይማኖቱ የቀና በቅናቱም ከከህዲዎች ጋር የሚጣላ በተቻለውም መጠን እነርሱን ለመገሠጽ የሚተጋ በአምልኮቱም በሥላሴ ስም የሚመከት ማመንና መታመን ጦሮቹና ቀስቱ የሆኑለት ጊዮርጊስ ተናገረው፡፡ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን ስሙ ለብቻው ከፍ ከፍ ብሏልና ለዘላለሙ አሜን ይሁን ይሁን ይደረግ ይደረግ ይጽና፡፡

........ /// ..........